# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 043 ጥቅምት 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## «የፍትሕ ዘርፉን ተአማኒነት ለመገንባት መዋቅራዊ ለውጥ ይደረጋል»

- ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር)
የፍትሕ ሚኒስትር



ዘሳለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የፍትህ ዘርፉን ተአማኒነት ለመገንባት መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚደረግ የፍትሕ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) አስታወቁ።

የፍትሕ ዘርፉን ተአማኒነትና ቅቡልነትን ለመገንባት የለውጥ ሥራዎቹ በትኩረት እንዲከናወኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰቧል።


ቋሚ ኮሚቴው ትናንት የፍትሕ ሚኒስቴርንና የተጠሪ ተቋማትን የሩብ ዓመት አፈጻጸም፣ የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ ዝግጅት ያለበትን ደረጃ እንዲሁም በፍትሕ ዘርፉ መሠረታዊ ለውጥ ሥራ ያለበትን ሂደት ገምግሟል።

ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርቱን ያቀረቡት ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር)፤ የፍትሕ ዘርፉን ተአማኒነት ለመገንባት የለውጥ ሥራዎች የሚከናወኑ መሆኑን አስረድተዋል።

ሆኖም የበጀት እጥረት፣ የሰው ኃይል ፍልሰት፣ በሥራ ጫና ክልሎች ወደተግባር ምዕራፍ አለመሸጋገር፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የጸጥታ ችግሮች ተግዳሮት ሊሆኑ እንደሚችሉ አመላክተዋል።

በፍትሕ ዘርፉ መዋቅራዊ ለውጥ ይደረጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤


«የፍትሕ ዘርፉን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡- ገበቦ ገብሬ

አምባሳደር ዣኦ ዥዩዋን

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቻይና ያደረጉት ጉብኝት ትልቅ ስኬት የተመዘገበበት ነው

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቻይና ያደረጉት ጉብኝት ትልቅ ስኬት የተመዘገበበት መሆኑን በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዣኦ ዥዩዋን ገለጹ፡፡

አምባሳደር ዣኦ ዥዩዋን ጉብኝቱን በተመለከተ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቻይና ያደረጉት ትልቅ ስኬት የተመዘገበበት ጉብኝት በዋናነት ሦስት ውጤቶች ተገኝቶበታል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ የኢትዮጵያና ቻይና ግንኙነት ከሁሉን አቀፍ ፅኑ ግንኙነት፤ ወደ ሁኔታዎች የማይፈታው ስልታዊ ትብብርና ወዳጅነት ደረጃ ከፍ ማለቱን በጋራ


ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ኢትዮጵያ በመርሆዎች መግለጫ ስምምነቱ ውይይት ውጤት ላይ መድረስ እንደሚቻል ታምናለች

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በመርሆዎች መግለጫ ስምምነት መሠረት በሚደረግ ውይይት አዎንታዊ ውጤት ላይ መድረስ እንደሚቻል ታምናለች ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሦስተኛው ዙር የዓባይ ግድብ ውሃ አሞላል እና ዓመታዊ የውሃ አለቃቀቅ ደንብ እና መመሪያን በሚመለከት የሚካሄደው የሦስትዮሽ ውይይት ትናንት ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም በካይሮ፣ ግብጽ ተጀምሯል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሦስትዮሽ ውይይቱን


ኢትዮጵያ በመርሆዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡- ገበቦ ገብሬ

## ‹‹ኢትዮጵያ ያሳትን የብዝሃ ማንነትና ተፈጥሮ ስፈጠራ ግብዓትነት ስመጠቀም በትብብር መሥራት ይጠይቃል››

- ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል
የሥራና ክህሎት ሚኒስትር

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ያላትን የብዝሃ ማንነትና ብዝሃ ተፈጥሮ ለፈጠራ ሥራ በግብዓትነት ለመጠቀም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንደሚጠይቅ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ፡፡

ዓለም አቀፍ የስታርትአፕ ሽልማት የአፍሪካ ጉባኤ ከጥቅምት 14 እስከ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ እንደሚካሄድም ጠቁመዋል።

ሚኒስትሯ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤


"ኢትዮጵያ ያሳትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










አቶ ሰብሃዲን ሱልጣን

# በመዲናዋ ለ300 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ለ300 ሺህ ዜጎች የሚሆን የሥራ ዕድል ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ የሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በቢሮው የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሰብሃዲን ሱልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት በሁለት ወራት ውስጥ ከ16 ሺህ በላይ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ለ300 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ተይዟል፡፡

የሥራ ዕድል ፈጠራው በአምስት የተለያዩ ዘርፎች ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በተለይ በኢንዱስትሪ፣ ማንፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን ላይ ልዩ ትኩረት መደረጉን አመላክተዋል።

በግብርና፣ በንግድ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩ ወጣቶች መኖራቸውንም ጠቁመው፤ የሥራ ዕድል ፈጠራውን ለማጠናከር ከመንግሥትና ከግል ተቋማት ጋር በትብብር እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ቀደም ሲል በጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ይሰጥ የነበረው ትኩረት አሁን ላይ በቋሚ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ተደርጓል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ወጣቶችን በኢንተርፕራይዝ ደረጃ በማደራጀትና በሌሎች ዘርፎች በማሰማራት የሥራ ዕድሎች እንደሚመቻቹ ገልጸዋል፡፡

ዕቅዱን ለማሳካት ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በመተባበር እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተጨማሪም የመሥሪያ ማሽነሪዎችንና የሰለጠነ የሰው ኃይል ከሚያቀርቡ ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር እንደ አንድ አቅጣጫ መያዙን አመላክተዋል፡፡

የውጭ ሀገራት የሥራ ዕድል በማመቻቸት ረገድ አሁን ላይ አዲስ የመዋቅር ለውጥ እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ በዘርፉ ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ኤጀንሲዎች ሕጋዊ ሆነው እንዲሠሩ እንዲሁም ዜጎች በቂ መረጃና ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል ብለዋል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት በተለያዩ አማራጮች ከ416 ሺህ በላይ የሥራ ዕድል መፈጠሩን ያስታወሱት ኃላፊው፤ እቅዱ አንፃር 90 በመቶ መሳካቱን ገልጸዋል፡፡

ወጣቱ ባለው ሙያ በመሰማራት ሥራዎችን ሳያማርጥ ዕድሎች መጠቀም ይገባዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ በተለያየ አጋጣሚ ከውጭ ሀገራት የተለያዩ የሥራ ዕድሎች ይመጣሉ፡፡ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየቀኑ እየጨመረ ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቅረፍ በዘላቂነት መሥራት አለባቸው፡፡

# ኤግዚቢሽኑ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለመሳብ ዕድል የሚፈጥር ነው

## - ከ85 ተቋማት በላይ ምርትና አገልግሎታቸውን እያስተዋወቁ ይገኛሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሳይንስ ሙዚየም እየተጎበኘ የሚገኘው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሆስፒታሊቲና ኤግዚቢሽን በቱሪዝም ልማት ዘርፍ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለመሳብ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ። በኤግዚቢሽኑ ከ85 ተቋማት በላይ ምርትና አገልግሎታቸውን እያስተዋወቁ ሲሆን፤ ከ200 ሺህ በላይ ጎብኚዎች እንደሚጠበቅ ሚኒስቴሩ ጨምሮ ገልጿል።

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሆስፒታሊቲና ኤግዚቢሽን በቱሪዝም ዘርፍ ተጨማሪ የአንቨስትመንት አማራጮች ለመሳብ ዕድል ይፈጥራል።

በኤግዚቢሽኑ የቴክኖሎጂና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምርቶቻቸውን ይዘው መቅረባቸውን አምባሳደር ናሲሴ ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር ናሲሴ ገለጻ፤ በኤግዚቢሽኑ በክልሎች የሚገኙ የተፈጥሮ፣ የባህል እንዲሁም የቅርስ ሀብት ለማወቅና እርስ በእርስ ለመተዋወቅ ይረዳል።

አምባሳደር ናሲሴ አክለውም፤ ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ ምድረ-ቀደምት ናት ከሚለው እሳቤ ጀምሮ የተለያዩ የቱሪዝም ሀብቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ በቀላሉ ለማስተዋወቅ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ እምቅ ሀብት ቢኖራትም ያሉትን ሀብት ባለማወቅ ልንጠቀምበት አልቻልንም ያሉት ሚኒስትሯ፤ ባለሀብቶች ኤግዚቢሽኑን ቢጎበኙ በዘርፉ ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጭ እንደሚያገኙ ጠቁመዋል።



አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በበኩላቸው የሀገርን መልካም ገጽታ በመገንባት የውጭ ባለሀብቶችን በዘርፉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል።

የተሻሻለ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ታሳቢ ተደርጎ ኤግዚቢሽኑ በተከፈተበት በመጀመሪያው ዕለት ከባለሀብቶች፣ ከግሉ ሴክተርና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የኢንቨስትመንት ፎረም ተካሂዷል።

ሚኒስትር ዴኤታው አክለውም ከኤግዚቢሽኑ ጎን ለጎን የቱሪዝም ልማቱን እንዲደግፍ የአምባሳደሮች ፎረም በቅርቡ ይካሄዳል ብለዋል።



አቶ ስለሺ ግርማ

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፉ ያላን እምቅ ሀብት ለማስተዋወቅ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽንና ሆስፒታሊቲ ላይ ትሳተፋለች።

ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ሀገር አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽን ባለማካሄዷ ዘርፉ ወደ ኋላ እንዲቀር አድርጎታል ያሉት አቶ ስለሺ፤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከጎብኚው ጋር የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንዲሁም ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽን ለማዘጋጀት ልምድ የሚወሰድበት መሆኑን ጠቁመዋል።

በኤግዚቢሽኑ ከ85 ተቋማት በላይ ምርትና አገልግሎታቸውን እያስተዋወቁ ሲሆን፤ ከ200 ሺህ በላይ ጉብኚዎች እንደሚጠበቅም ነው አቶ ስለሺ የተናገሩት።

# የቃጠሎ መድህን

**ውብሸት ሰንደቁ**

ምድር ገሀነብ የሆነችባቸው ሕፃናት፤ ከውጭ ሲያዩት ሠላማዊ በሚመስለው ሆስፒታል ውስጥ እዚህም እዚያም ተኝተዋል። ከብላቴንነታቸው፤ ከማሕፀን ብቅ ከማለታቸው ሕይወት ፍሟን አርገብግባ፤ ውሃዋን አፍልታ ዕምቡጥ ገላቸውን የተቀበለቻቸው ናቸው። በአርባ ምንጭ ከሆስፒታሉ የቃጠሎ ሕክምና ክፍል ይህ ትዕይንት እንግዳ አይደለም።

በማዕከሉ የቃጠሎ ሕክምና ክፍል ካገኘናቸው አንዷ ሕፃን ሮሐማ ኢንድርያስ ትበላለች። የአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጨቅላ ነች። ዕምቡጥ ገላዋ ነድዶ በነጭ ፋሻ ተጀቡኗል። ከትከሻዋ ገደማ ተነስቶ እስከ ጭኖቿ በፈላ ውሃ ነፍራለች። የእስትንፋስ ማገዣ ተደርጎላታል። የተዥጎረጎረ ገላዋ በተንፈቀፈቀበት የፈላ ውሃ እንደቲማቲም መላላጡን አይደብቅም። ያንጨረጨረውን የፍም እሳት መርገምት ዓይን አውጥቶ ይናገራል።

የሕፃን ሮሐማ እናት ሕይወት ፅዶላ አርባ ምንጭ አካባቢ ነው የሚኖሩት። የቤት ውስጥ ሥራዎችን እየሠሩ ነበር። ውሃ እያፈሉ፤ ጎን ለጎን ሌላም ሥራ እየከወኑ። የፈላ ውሃቸውን ከምድጃ አውርደው ለሌላ ሥራ ደጅ ይወጣሉ። በዚህ አጋጣሚ ነበር ጨቅላ ልጃቸው ሮሐማ ከመደብ ተንሸራትታ የፈላ ውሃ ውስጥ የገባችው። የጨቅላ ልጃቸውን እሪታ ሰምተው ሮጠው የገቡት እናት ያዩትን ማመን አልቻሉም። ልጃቸው በፈላ ውሃ ነፍራለች።

በአርባ ምንጭ አካባቢ ነዋሪዎች ዘንድ ይህ የጨቅላ ሮሐማ ገጠመኝ ብቻ አይደለም። ብላቴና እንዳልከው ጌቱም የዚህ ገፈት ቀማሽ ነው። ሙሉ አካሉን ይዞ መጥቶ ሕይወት በእሳት ያጎደለችው የአንድ ዓመት ሕፃን በሚድህበት ጊዜ ቤት ውስጥ ከሚነድ ምድጃ ተንሸራቶ ገብቶ ነው ቃጠሎ የደረሰበት። ሕፃኑ በተለይ ሁለቱ እግሮቹ እንደማገዶ ጨሰዋል፤ ተቃጥለዋል። በዚህም ሕፃን እንዳልከው በአርባ ምንጭ ሆስፒታል ቃጠሎ ሕክምና ማዕከል ለሰባት ወራት ያህል ተኝቶ እየታከመ ነው።

እናት አቴነሽ ማና በአካባቢው አልነበሩም። ልጃቸውን ለቤት ሠራተኛ አምነው ሰጥተው ነበር። አደራ የተቀበለችው ሠራተኛ እንቅልፍ በጣላት አፍታ ነው ሕፃኑ እሳት ውስጥ የገባው። ጎረቤት ተሯሩጦ ልጁን ወደ ሆስፒታል ባያመጣው ኖሮ ጉዳቱ የከፋ ይሆን እንደነበር ይናገራሉ።

ከፍተኛ ጉዳት ያስተናገዱት እግሮቹም መንቀሳቀስ፤ መታጠፍና መዘርጋት መጀመራቸውን ያነሳሉ። ምስጋና ለሕክምና ባለሙያዎች እና ስፔሻሊስቶች ይሁንና አሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እናት ያስረዳሉ።

ታዳጊ ቤተልሄም ዓለሙ ሌላዋ የ14 ዓመት ገደማ ጉብል ናት። ሙሉ ፊቷ ያልጠገገ የእሳት ለምፅ ይታይበታል። ዓይኖቿ በተዓምር ይትረፉ እንጂ አፍንጫዋና ቅንድቧ በፍም ሟምተዋል። ከንፈርና ፀጉሯ፤ ሽፋሽፍትና ጆሮዎቿ እላዩዋ ላይ ከስለዋል። ለጋነት ብቅ ከማለቷ በነዲድ እሳት ከስማለች።

ታዳጊ ቤተልሄም የሚጥል በሽታ አለባት። ኩሽና ውስጥ የዕለት ሥራዋን እየከወነች ነበር። እሳቷን አቀጣጥላ ጉድ ጉድ በምትል ጊዜ ነው እሳት ላይ የወደቀችው። ለእሳት የተዳረገችው በቤት ማንም ባልነበረበት ወቅት ነውና ለደቂቃዎች በፍም እሳት ተቃጥላለች።

አረመኔው እሳት ያከሰመው የለጋነት ፊቷንና ፈገግታዋን ብቻ አልነበረም። ሲሦ የሚጠጋውን ለጋ አካሏን አዳርሷል። ምሥጋና ለሆስፒታሉ የዘርፉ ስፔሻሊስቶች ይግባና ከሌላ የአካል ክፍሎቿ ላይ እየተወሰደ እንድታገግም እየታገዘች ትገኛለች። ከሁለት ወራት ተኩል ሕክምና በኋላም ጥሩ መሻሻሎች ላይ ደርሳ መንቀሳቀስ ሁሉ ጀምራለች።

ዶክተር ኤፍሬም ጋሻው ጀነራል ሰርጀሪ እና ፕላስቲክና ሪኮንስትራክቲቭ ሰብ ስፔሻሊቲ ሰርጀሪ ባለሙያ ናቸው። በአርባ ምንጭ ሆስፒታል የቃጠሎ ሕክምና ማዕከል እያገለገሉ ነው የሚገኙት።

የቃጠሎ ሕክምና ዘርፍ ትኩረት የተነፈገው ነው። ለዚህም ማሳያ በሆስፒታሎች የቃጠሎ ሕክምና ማዕከል አለማቋቋማቸው እና የባለሙያዎች በብዛት ያለመኖር ይላሉ ባለሙያው። በሀገሪቱ ከ50 የማይበልጡ የዘርፉ ስፔሻላይዝ መኖራቸውንም እንደማሳያ ያነሳሉ።

መንግሥት ትኩረት የነፈገው ዘርፍ ከመሆኑም ሌላ ሕክምናው ረጂም ጊዜን የሚፈልግ በመሆኑ የግሉ ዘርፍ እንዳይገባበት ያደርገዋል ባይ ናቸው።

የቃጠሎ ሕክምና ዘርፍ ትኩረት ባለመሰጠቱ በርካታ ሰዎች ላይ ጉዳት ይደርሳል ይላሉ። የሕክምና ማዕከሉ በአካባቢው የሚገኝ ብቸኛው በመሆኑ የቃጠሎ ሕክምና ተገልጋዮች እንደሚበዙም ይናገራሉ። በደቡቡ የኢትዮጵያ ክፍል ከሚገኙ በርካታ ሆስፒታሎች ሪፈር ተፅፎላቸው የሚመጡ ታካሚዎች ብዙ መሆናቸውንም ያብራራሉ።

በቃጠሎ በተለይ ሕፃናት እና የሚጥል በሽታ ያለባቸው ሰዎች ተጋላጭ እንደሆኑ የሚናገሩት ዶክተር ኤፍሬም፤ ለቃጠሎ ሕክምና ወደ ሆስፒታሉ የሚመጡትም 70 በመቶ የሚሆኑት ሕፃንነት ዕድሜ ውስጥ ናቸው። የሚጥል በሽታ ያለባቸው ሰዎችም በዚሁ ልክ ተጋላጮች ናቸው ሲሉ ያስረዳሉ።

የቃጠሎ ሕክምና በማንኛውም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችል ቢሆንም እንኳን ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም ሕፃናትንና የሚጥል በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ልዩ ጥንቃቄ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ይመክራሉ። ቃጠሎ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ አደጋው የደረሰባቸውም በፍጥነት ወደ ሕክምና መሄድ ይኖርባቸዋልም ይላሉ።

በአርባምንጭ ሆስፒታል የቃጠሎ ሕክምና ማዕከል አስተባባሪ የሆኑት ተመስገን አሸብር የዶክተር ኤፍሬምን ሃሳብ ይጋራሉ። ዘርፉ ትኩረት የተሰጠው ባይሆንም በሆስፒታሉ የቃጠሎ ሕክምና ማዕከል ተመስርቶ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ እንደሆነ ነው የሚያነሱት።

በሁለት ዓመት ገደማ ውስጥም ሆስፒታሉ ማዕከሉን ካቋቋመ 300 የሚጠጉ የቃጠሎ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ሕክምና ሰጥቷል ይላሉ። ከሲዳማ እና ኦሮሚያ አጎራባች ክልሎች የመጡትን ጨምሮ የክልሉን ሕዝብ እያገለገለ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ታካሚዎች አብዛኞቹ ሕፃናት ናቸው። በዚህ ምክንያትም ሃኪሞች በሕክምና ጊዜ እንደሚቸገሩ ገልጸው፤ የሕክምናውን መንገድ አዘምኖ ህመም አልባ የማድረግ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ያብራራሉ። የማዕከሉን ታካሚዎችን የመቀበል አቅም ለማስፋትም እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውንም አጫውተውናል።

በሀገሪቱ ያለው የእሳት አደጋን የመከላከል አቅም ግንባታ እምብዛም በሆነበት በዚህ ዘመን ተጋላጮቹ ሕፃናት እና የሚጥል በሽታ ያለባቸው ሰዎች ናቸው እና እንዲህ መሰል የቃጠሎ ሕክምና ተቋማት ሊስፋፉ ቢችሉ ትውልድን ማዳን ይሆናል። በእርግጥም መሰል የሕክምና ማዕከላትን ማስፋፋት ለዕንቡጦች የቃጠሎ መድህን ማዘጋጀት እንደሆነ የሚቆጠር ነው።

# የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል የቴክኖሎጂ ባለቤትነት አቅምን መገንባት ያስፈልጋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል የቴክኖሎጂ ባለቤትነት አቅምን መገንባት እንደሚያስፈልግ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አስታወቀ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት 4ተኛው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት የፓናል ውይይት አካሂዷል። ከጥቅምት 12 ቀን እስከ 15 /2016 ዓ.ም የሚቆይ ዐውደ ርዕይ በጊዮን ሆቴል ተከፍቷል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ሰለሞን ሶካ እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያን የመሰሉ ሀገራት ሌሎች ሀገራት ያመረቷቸውን ቴክኖሎጂዎች እየተጠቀሙ ይገኛሉ። ይህም በብሔራዊ ደህንነታቸው ላይ ስጋት እየፈጠረ ነው። ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም የቴክኖሎጂ ባለቤትነት አቅምን መገንባት ያስፈልጋል ብለዋል።



አቶ ሰለሞን የነገውን ትውልድ የሳይበር ደህንነት ለማጎልበት ጥናቶችና ምርምሮችን ማበረታታት፣ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ የግል ተቋማትን ማበረታታት እንዲሁም ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ መፍጠር ላይ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ማንኛውም ቴክኖሎጂ የሚጠቀም ሰው ለሳይበር ጥቃት የመጋለጥ ዕድሉ ሰፊ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊና ማጎልበት ላይ እየተሠራ መሆኑንም አንስተዋል።

የሳይበር ጥቃት ድንበር የለሽ፣ ውስብስብና የማይገመት በመሆኑ አንድ ሀገር የሳይበር ደህንነት አቅሙን ካላሳደገ ከፍተኛ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ በመግለጽ፤ ይህንን ለመከላከል መረጃንና የመረጃ መሠረተ ልማቶችን ከሳይበር ጥቃት መጠበቅ፣ ከቴክኖሎጂ ጥገኝነት መላቀቅና የቴክኖሎጂ ባለቤትነት አቅም መገንባትና ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ አስገንዝበዋል።

የመከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ በበኩላቸው አሁን ባለው የዓለም ነባራዊ ሁኔታ የሳይበር ቴክኖሎጂ የሀገራት ትልቁ የመወዳደሪያ አቅም መሆኑን ተናግረዋል።

የሳይበር ጥቃቶች ብሔራዊ ደህንነት ላይ ስጋት መፍጠራቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ቁልፍ የመሠረተ ልማት ተቋማት የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ እንደ መደበኛ ሥራቸው ትኩረት ሰጥተው ሊከውኑት የሚገባ ተግባር ነው ብለዋል።

ዶክተር አብርሃም የኢትዮጵያ ዲጂታል 2025ን ዕቅድ እውን ለማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግሩ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ ሳይበር ደህንነት ተጋላጭነትን ለማስወገድ ቴክኖሎጂዎችን በራስ አቅም መገንባትና በፈጠራ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ታዳጊዎችን ማበረታታት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

ሚኒስትሩ በአሁኑ ጊዜ የሳይበር ቴክኖሎጂ በዓለም ላይ ዋነኛ መወዳደሪያ እንደመሆናቸው የሳይበር ወንጀሎችም ዋነኛዎቹ ስጋቶች መሆናቸውን ተናግረዋል።

# ለ100 ሺዎች እንጀራ ያቀረበው ምጣድ

**ተስፋ ፈሩ**

ብዙ ዓይነት ዐውደ ርዕዮች ይካሄዳሉ። የስዕል፣ የፎቶግራፍና የመጽሐፍት ዐውደ ርዕዮች የተለመዱ ናቸው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የጤና፣ የንግድ፣ የቱሪዝም ወዘተረፈ እየተባለ በየዘርፉ የሚካሄዱ ዐውደ ርዕዮች ተበራክተዋል። ለሀገራችን እንግዳ ከሆኑ የዐውደ ርዕይ ዓይነቶች አንዱ «የሥራ ገበያ» ዐውደ ርዕይ ነው።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ከደረጃ ዶት ኮምና ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር በየዓመቱ የሚያዘጋጀው የሥራ ገበያ ዐውደ ርዕይ ላለፉት አምስት አመታት በክልል ከተሞችና በአዲስ አበባ ሲካሄድ ቆይቷል። ዐውደርዕዩ በእስካሁኖቹ መድረኩ በድምሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል በማመቻቸት እንጀራቸውን ያቀረበ ምጣድ ሆኗል።

ዘንድሮም ከ20ሺ በላይ አዲስ ተመራቂ ተማሪዎችና ከ200 በላይ ከተለያየ ዘርፍ የተውጣጡ ቀጣሪ ድርጅቶች የተሳተፉበት ሥራ ፈላጊዎችንና ቀጣሪ ድርጅቶችን ያገናኘ ዐውድ ርዕይ ባሳለፍነው ሳምንት በሚሊኒየም አዳራሽ ተካሂዷል። መድረኩ በተለያዩ የሥራ መስኮች ስድስት ሺ የሚደርሱ የሥራ ዕድሎች የተፈጠሩበት ነው።

አዲስ ተመራቂዎችን ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት፤ የምልመላ ሂደትን በማቀላጠፍ ብሎም ተቀጣሪዎችንና ቀጣሪ ድርጅቶችን ውጤታማ በማድረግ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትም ተነግሮለታል። በአካል በመገኘት መሳተፍ የማይችሉ ተመራቂዎችም በየነመረብን በመጠቀም እንዲሳተፉ የተደረገበት ሆኗል።

ትንሳኤ ጌቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች። ከመመረቋ በፊት በምትማርበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተዘጋጅቶ በነበረው አዲስ ተመራቂዎችንና ሥራ ቀጣሪዎችን ማገናኛ አውደ ርዕይ ከሦስት ወር በኋላ ተመራቂ መሆናን ጠቅሳ ጥቂት ድርጅቶች ጋር ተመዘገበች። ከተመረቁ ከአንድ ወር በኋላ ከአንዱ ድርጅት ስልክ ተደወለላትና የጽሑፍና የቃለ መጠይቅ ፈተናዎችን አልፋም ለመቀጠር በቃች።

ሥራ ከጀመረች ከአንድ ወር ተኩል በላይ ቀን የሆናት ትንሳኤ፣ በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው ዐውደ ርዕይ ላይ የተገኘችው የሰው ኃይል አስተዳደር ሠራተኛ ሆና የምትሠራበት ድርጅት አዲስ ሠራተኞችን ለመቅጠር የያዘውን ውጥን ለማሳካት ነው።

የእርሷን ሥራ ማግኘት የሰሙ ብዙ ጓደኞቿ ወደ ዐውደ ርዕዩ ይመጣሉ ብላ ተስፋ ያደረገችው ወጣቷ፣ «ይሄ ዕድል መዘጋጀቱ በጣም ጥሩ ነው፤ አንዷ ተጠቃሚ በመሆኔም ደስተኛ ነኝ። በጣም ብዙ ሥራ ያላገኙ ወጣቶች አሉ። በተለይ በዚህ አመት መንግሥት የአዲስ ሠራተኛ ቅጥር አይፈጽምም መባሉ አስጨንቆን ነበር። በበኩሌ ይህን ዕድል ስላገኘሁ መድረኩን ያዘጋጁትን አካላት ማመስገን እፈልጋለሁ።» ብላለች።

የትምህርት ማስረጃውን ለቀጣሪ ድርጅቶች ለማስገባት ሲታተር የነበረው ገዛኸኝ ቶላም አዲስ ተመራቂ ነው። በኬሚስትሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዟል። የእግር ጉዳት ያለበት ወጣቱ፤ እንደዚህ ዓይነት መድረክ መመቻቸቱ ለተመራቂ ተማሪዎች ትልቅ ዕድል ነው፤ በተለይ ለአካል ጉዳተኞች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ይላል።

አካል ጉዳተኞች ሥራ ለመፈለግ ሲንቀሳቀሱ ብዙ ችግር ያጋጥማቸዋል ያለው ገዛኸኝ፣ «በተለይም እንደ እኔ የእግር ጉዳት ላለበትና በሁለት ክራንች ለሚንቀሳቀስ ሰው፣ መንገዶች ምቹ ስላልሆኑ ቀጣሪ ድርጅቶቹ ያሉበት ድረስ ሄዶ ማመልከት በጣም አስቸጋሪ ነው» በማለት በመቶዎች የሚቆጠሩ ድርጅቶች በአንድ ቦታ ተሰባስበው ማግኘቱ ብዙ ውጣ ውርድ እንዳቀለለለት ይናገራል።

ሌላኛዋ በዐውደ ርዕዩ ላይ የተገኘችው ተመራቂ ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪዋን የያዘችው ሰሚራ አህመድ ነች። ዐውደ ርዕዩን በጣም ወድጄዋለሁ የምትለው ሰሚራ፣ 10 ድርጅቶች ጋር አመልክቼ በተለይ አንዱ ድርጅት ይቀበለኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ስትል ተናግራለች።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና የሥነ-ተግባቦት ትምህርት ክፍል ምሩቁ መስፍን ከተማ በበኩሉ የዐውደ ርዕዩን ፋይዳ ሲገልጽ፣ በርካታ ድርጅቶች በአንድ ቦታ ተሰባስበው መገኘታቸው ብዙ ጥቅም አለው። ብዙ ምርጫ ስለሚኖር በአንድ ጊዜ ብዙ ድርጅቶች ጋር ማመልከት ይቻላል፤ ይበልጥ መረጃ ለማግኘትም ያግዛል ብሏል።

ጸጋዬ ታደሰ (ዶ/ር) የሞርቴክ ኢንዱስትሪ ፒ ኤልሲ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ናቸው። ድርጅታቸው ለኢትዮጵያ የሳይንስ ማኅበረሰብ የሚያገለግሉ ሳይንሳዊ ዕቃዎችን ከውጭ አስመጪ ነው። የውጭ ሀገር ልምዶች እንደሚያሳዩት የሥራ ቅጥር ዐውደ ርዕይ ለብዙ ተማሪዎች ዕድል ይፈጥራል።

ለቀጣሪ ድርጅቶችም የተሻለ ብቃት ያላቸውን ሠራተኞች እንዲገኙ ይረዳቸዋል ይላሉ። ድርጅታቸው በዐውደ ርዕዩ ላይ ሲሳተፍ የመጀመሪያው መሆኑን በመጥቀስም የተሻሉ ሠራተኞችን እናገኛለን ብለው ተስፋ እንዳደረጉ ይናገራሉ።

የትምህርት ጥራቱ ወድቆ ስለነበረ ገበያው ላይ የተሻለ ብቃት ያላቸው ሰዎችን ማግኘት አልቻልንም የሚሉት ዶክተሩ፣ «የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ ስናወጣ አንድ ሺ አመልካቾች ቀርበው ከእነዚያ ውስጥ ሁለት ሦስት ማውጣት ከባድ የሚሆንበት ጊዜ አለ። መንግሥት የተሻለ የሰው ኃይል ማፍራቱ ላይ መሥራት አለበት።» በማለት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸው ያሳስባሉ።

በዐውደ ርዕዩ ላይ እየተሳተፈ የሚገኘው ከ10 ሺ በላይ ሠራተኞች ያሉት የቀርጫንሼ ግሩፕ የቅጥርና ዝውውር ሥራ ክፍል ኃላፊ አቶ ጌዲዮን አቶምሳ በበኩላቸው፣ መድረኩ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። ድርጅታችን ከዚህ ቀደም በተካሄዱት ዐውደ ርዕዮች 270 ሠራተኞችን ቀጥሯል። በዚህኛው መድረክ ደግሞ 60 ሠራተኞችን ለመቅጠር ዕቅድ ይዘናል ብለዋል።

ለሁለት ቀናት የቆየውን ዐውደ ርዕይ መርቀው የከፈቱት የሥራ እና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ንጉሡ ጥላሁን ሚኒስቴር መሥሪያቤታቸው ባለፉት አመታት ከደረጃ ዶት ኮምና ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ባዘጋጃቸው የሥራና ሠራተኛ ማገናኛ መድረኮች በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል ማግኘታቸውን ገልጸዋል።

የተማሪዎችን የመቀጠር ብቃት ማሳደግ እንዲቻልም ለተመራቂ ተማሪዎችና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ሲሰጡ መቆየታቸውንም አስታውሰዋል።

መድረኩ የሥራ ዕድልን ከሥራ ፈላጊዎች ጋር በወቅቱ ለማገናኘት እንዲሁም የሥራ ገበያውን አቅርቦትና ፍላጎት ለማጣጣም ያስችላል ያሉት አቶ ንጉሡ፤ ሥራ ፈላጊዎችንና ቀጣሪ ድርጅቶችን የሚያገናኙ ተመሳሳይ መድረኮች ወደፊትም ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

# ትውልዱ ችኮላን በመተው ችግሮቹን በውይይት በመፍታት ሀገራዊ አንድነቱን ሊያስቀጥል ይገባል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የአሁኑ ትውልድ ችኮላን ወደ ጎን በመተው ችግሮችን በውይይት በመፍታት ሀገራዊ አንድነቱን ሊያስቀጥል ይገባል ሲሉ የሀገር ሽማግሌዎችና የተለያዩ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ።

የጋሞ የሀገር ሽማግሌ የሆኑት አቶ አመለ አልቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ወጣቶች በቤተሰብ፣ በመንደርና በሀገር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመነጋገር እየፈቱ አንድነታቸውንና ሠላማቸውን ማጠናከር አለባቸው።



አቶ አመለ አልቶ

ኢትዮጵያውያን ተዋልደው የሚኖሩ ሕዝቦች በመሆናቸው ግጭቶችን በመነጋገር በመፍታት አንድነት ማስቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል።

አባቶች ሲመክሩና ሲቆጡ እሺ የሚል ወጣት እንደሀገር ያስፈልገናል ያሉት አቶ አመለ፤ ችግሮች ሲያጋጥሙ አባቶች ወጣቱን በመምከር ወደ ሠላም መመለስ እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።



አቶ ሞናዬ ሞሶሌ

ሠላም በመተጋገዝ፣ በመከባበርና በአብሮነት የሚመጣ መሆኑን ጠቁመው፤ ችግሮችና ከማባባስ ይልቅ ማስተካከልና ሠላምን መፍጠር ተገቢ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከወጣቶችና ከጎልማሶች የሚጠበቀው ሀገራዊ አንድነትንና ሠላምን ማስቀጠል መሆኑን የገለጹት አቶ አመለ፤ ጦር ያነሱ ዜጎች ስለሠላም ሲሉ ነፍጣቸውን ዝቅ አድርገው ለውይይት መቀመጥ እንዳለባቸው ተናግረዋል።

የሠላም እጦት ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ የሚያጠፋ መሆኑን በመግለጽ፤ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ሁሉ ወደ መነጋገር ሲመለሱ መንግሥትም በሆደ ሰፊነት መድረክ የሚፈጠርበት መንገድ መቻቻት እንዳለበት ገልጸዋል።

ኢትዮጵያውያን በሠላም መኖር ይፈልጋሉ ያሉት የሀገር ሽማግሌው፤ ወጣቶች ሀገርን የሚጠቅም አቅማቸውን ለማጎልበት ሠላማዊ ሕይወታቸውን ሊያጠናክሩ ይገባል ብለዋል።

ሌላኛው የሀገር ሽማግሌ አቶ ሞናዬ ሞሶሌ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያውያን የመተሳሰብና የመከባበር ባህላቸውን በመጠበቅ ሠላማቸውን ማስጠበቅ አለባቸው።

እንደ ሀገር ወጣቶች አባቶቻቸው ያቆዩትን የአንድነትና የወንድማማችነት ባህል አጠናክረው በማስቀጠል ችግሮቻቸውን ለመፍታት መዘጋጀት አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ችግሮቻቸውን በመተሳሰብ ማለፍና በጋራ የመኖር ባህል እንዳላቸው ጠቅሰው፤ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎችና የሃይማኖት አባቶች ወጣቱን በቀና መንገድ ሊመሩና ሊመክሩ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የዶዶላ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ጌጤ ቱራቃበቶ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሀገርን ማስቀጠል የሚቻለው በመቻቻልና በመነጋገር በመሆኑ የአሁኑ ትውልድ ችኮላን በመተው ሀገርን የሚጠቅም ሥራ ላይ ማተኮር ይገባዋል።

ወጣቶች ሠላማቸውን መጠበቅና ፍቅርን መስበክ አለባቸው ያሉት ወይዘሮ ጌጤ፤ በየትኛውም አካባቢዎች ላይ የሠላም ድርሻ ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ይገባል ብለዋል።

ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ሠላሙን መጠበቅ ግዴታው መሆኑን ጠቁመው፤ ደስታም ሆነ ኀዘን ማሳለፍ እንዲሁም ልማትን ማረጋገጥ የሚቻለውም ሀገር ሠላም ስትሆን ነውና ወጣቱ ሰከን ብሎ ስለነገው ሊያስብ ይገባል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

የባቱ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኢማምጎሴ ዲልበቶ ደግሞ፤ ዜጎች ሠላማቸውን አስጠብቀው በመቻቻል ሊኖሩ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደዜጋ ችግሮች ካሉ በውይይት ለመፍታት መጣርና ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በመቻቻል መኖር እንደሚገባ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያውያን እንደቤተሰብ የኖሩ በመሆናቸው አንድነቱን አስጠብቆ መጠቀል እንደሚገባ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያውያን በልማት፣ በትምህርትና በቤተሰብ ልማት ላይ አተኩረው ሊሠሩ ይገባል ያሉት አቶ ኢማምጎሴ፤ አባቶች ልጆቻቸውን በማስተማር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲመጣ ማድረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል።

# በዞኑ ሕገወጥ ስደትን ለመቆጣጠርና ለመቀነስ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ተደርጓል

**ታደሰ ብናልፈው**

<u>ሆሳዕና፡-</u> ሕገወጥ ስደትን ለመቆጣጠር በሥራ ፈጠራ ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ እያከናወነ መሆኑን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሀዲያ ዞን የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት መምሪያ አስታወቀ፡፡

የመምሪያው የገጠር ዘርፍ ኃላፊ አቶ ኤፍሬም አማኑኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት ከሀዲያ ዞን በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ዐረብና ደቡብ አፍሪካ የሚሰደዱ ወጣቶችን ቁጥር ለመቀነስና ከስደት ለማስቀረት በሥራ ፈጠራ ዘርፍ ላይ የተጠናከረ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

የወጣቶችን የስደት ቁጥር ለመቀነስና ለማስቀረት እየተሠራ ባለው ሥራም ከ35 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ ዕድል ይፈጠርላቸዋል ብለዋል፡፡

በዞኑ በ2015 በጀት ዓመት ሥራአጥ ወጣቶችን ወደ ሥራ በማሰማራት ከስደት ለመከላከል 125 ኢንተርፕራይዞችን በገጠር በተለያዩ ዘርፎች መሳተፋቸውን አስታውሰው፤ በተያዘው በጀት ዓመትም የወጣቶችን የሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የስደተኞችን ቁጥር ለመቀነስ ከ250 እስከ 300 የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ ዘርፎች የማሰማራት ሥራ ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲሉ አመላክተዋል፡፡

በዞኑ ካለው የወጣት የሥራአጥ ቁጥር አንፃር እየተሠራ ያለው የሥራ ዕድል ፈጠራ በቂ አይደለም ያሉት አቶ ኤፍሬም ወጣቶችን የሥራ ዕድል በመፍጠር በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ በስፋት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዞኑ በተለያዩ ዘርፎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ሥራአጥ ወጣቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የማድረግና ከስደት የማስቀረት ሥራ በትኩረት እንደሚሠራበት ገልጸዋል፡፡

በሀዲያ ዞን የሚገኙ የገጠርና የከተማ ሥራ አጥ ወጣቶችን በተለያዩ የሥራ መስኮች የማደራጀት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ እየተሠራ ያለውም


አቶ ኤፍሬም አማኑኤል

ሥራ ለወጣቱ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ወጣቱ ወደ ዐረብ ሀገራትና ደቡብ አፍሪካ የሚያደርገውን ስደት ለመቀነስ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

በገጠር የሚገኙ የዞኑ ሥራአጥ ወጣቶችን በግብርና ዘርፉ ማለትም በስንዴ፣ በጤፍ፣ በገብስና በድንች ምርት፤ በዶሮ እርባታ፤ በእንስሳት ድልብና በማር ምርት በማደራጀት በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የማድረግ እየተሠራ ነው መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ወጣቱን ከስደት ለማስቀረት ትልቅ አስተዋፆ አለው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ዞኑ በወጣቶች ሕገወጥ ስደት የሚታወቅ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ የወጣቶችን ሕገ ወጥ ስደት ለማስቀረት ለከተማና ለገጠር ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የሥራ ዕድል እየተፈጠረላቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

# ‹‹ኢትዮጵያ ያላትን የብዝሃ ማንነትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ የብዝሃ ተፈጥሮና ማንነት ያላት አገር ናት። ብዝሃነት ደግሞ ለፈጠራ ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ ነው። ያለን ብዝሃነት ለፈጠራ ለመጠቀም ማልማት፣ መኮትኮትና መበልጸግን የሚጠይቅ ስለሆነ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ የሚጠይቅ ነው።

የሥራ ፈጠራን ለማስፋት አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አቅሞችን ማስተባበርን ይጠይቃል ያሉት ሚኒስትሯ፤ አሁን ላይ የፈጠራው ዓለም ፍጥነት በተሞላበት ዕድገት ውስጥ ይገኛል።ኢትዮጵያም ያላትን እምቅ አቅም አሟጦ ለመጠቀም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በትብብር መሥራት እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ አፍሪካ የወጣቶች አህጉር ናት። ይህን መልካም አጋጣሚ በአዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎች ማገዝና ጀማሪ ቢዝነሶችን አጎልብቶ ጠንካራ ተወዳዳሪነትን መፍጠር ይጠይቃል። ‹ከግሎባል ኢኖቬሽን ኢንቬቲቭ ግሩፕ› ጋር በመተባበር የተዘጋጀው ዓለም አቀፍ የስታርትአፕ ሽልማት የአፍሪካ ጉባኤም ዓለም አቀፋዊ ትብብርን በማሳደግ አዳዲስ አጋር አካላትን ለማፍራትና በአፍሪካ ደረጃ በጀማሪ የንግድ ስራዎች ላይ ፈጠራን ማዕከል ያደረጉ ወጣቶችን ለማበረታታት ያግዛል።

የኢትዮጵያን ትክክለኛ ገጽታ ለሌላው ዓለም በማስተዋወቅ ወደ አህጉርና ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ገበያ ለመግባት ዕድል እንደሚፈጥርም ጨምረው ገልጸዋል።

ዓለም አቀፍ የስታርትአፕ ሽልማት የአፍሪካ ጉባዔ በአዲስ አበባ በሳይንስ ሙዚየም ከጥቅምት 14 እስከ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በሳይንስ ሙዚየም እንደሚካሄድ ጠቅሰው፤ በጉባዔው ከ300 በላይ አህጉር አቀፍ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለቤቶች ይወዳደራሉ። ከእነዚህ ውስጥ የተሻለ ሥራ ይዘው ለቀረቡ 15 ተወዳዳሪዎች ሽልማት ይበረከታል። በዚህም የልምድ ልውውጥ የሚደረግበትና ዓለም አቀፍ ትስስርን ለማጠናከር እንደሚያግዝም ጠቁመዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በጋራ ያዘጋጁት “ኔክስት ኢትዮጵያን ስታርትአፕ ኢኒሼቲቭ” መርሃ ግብር ዛሬ ጥቅምት 13 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ ገልጸው፤ ይህም ለቴክኖሎጂ ልማት ምቹ ሥነምህዳር ለመፍጠር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አመልክተዋል።

# «የፍትሕ ዘርፉን ተአማኒነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በኅብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎች፣ ሮሮ እና በአገልግሎት ርካታ ማጣት ችግሮችን ለመቅረፍ ትኩረት ይደረጋል ብለዋል።

የዘርፉን ተአማኒነት እና ቅቡልነት ለማሳደግ የሚሠራው ሥራ ማኅበረሰብ ተኮር እንደሚሆን እና ባህላዊ አሠራርን ከዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓት ጋር በማቀናጀት በኢትዮጵያ የመሠረተ ማኅበረሰብ ፍትሕ ማምጣት ላይ እንደሚያተኩርም ጠቁመዋል።

የለውጥ ሥራው የፍትሕ ዘርፍ ባለሙያዎች እና አመራሮች ከብቃት እና ሥነ ምግባር ጋር ተያይዞ ያሉባቸውን ክፍተቶችን ማጥራት ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል። ለትግበራው የሕግ ማዕቀፍ መዘጋጀቱንም ነው የተናገሩት።

የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ ማዕቀፍ ሂደቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ እየተገባደደ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በማረሚያ ቤቶች ከታራሚዎች አያያዝ ጋር ተያይዞ በበጀት እጥረት ምክንያት ይነሳ የነበረውን ቅሬታ ለመፍታት ቅድሚያ ተሰጥቶት ምላሽ መሰጠቱንም ተናግረዋል።

ከህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተገናኘ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚመለከት የምርመራ ክስ መመሪያ መዘጋጀቱን የጠቆሙት ዶ/ር ጌዲዮን፤ ከባለድርሻ አካላት የተገኘውን ግብአት በማስተካከል ወደ ትግበራ ይገባል ብለዋል።

የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማዘመን የተቀናጀ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን አጠቃቀም ይተገበራል፣ ልምድና ለሙያዎች ቀናኢ የሆኑ ባለሙያዎችን የሥራና የኑሮ ሁኔታ ማሻሻያ በማካሄድ በተቋሙ እንዲቆዩ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

የአስተዳደር ፍትሕን ሥርዓቱን ማዘመንና ቀልጣፋ ማድረግ፣ የዘርፉን ተአማኒነት የማሳደግ ተግባራት በትኩረት እንደሚተገበሩም አመልክተዋል። የለውጥ ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ የተቋም ግንባታና የሪፎርም ዘርፍ በማደራጀት እየተመራ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ እጸገነት መንግሥቱ በበኩላቸው፤ የለውጥ ሥራዎቹ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተተገበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻሉን አመልክተዋል። የምክር ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ትግበራ አካል እንደሆነም ገልጸዋል።

በለውጡ ሂደት ወደ ሽግግር ምዕራፍ ያልገቡ ክልሎች እንዲገቡ ክትትልና ግፊት እንደሚደረግ አመልክተዋል። በፍትሕ ዘርፍ ለሚተገበሩ አጠቃላይ የለውጥ ሥራዎች እና ለሂደቱ ስኬታማነት ድጋፍ ይደረጋልም ብለዋል።

በመዝገብ ማጥራትና ማስቀጣት ምጣኔ፣ ዓለም አቀፍ ትብብርን የማጠናከር ጅምር ሥራዎች፣ ተቋሙን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማደራጀት ተግባራት አፈጻጸምን በበጎነት በመገምገም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አሳስቧል።

የሕግ ረቂቅ ሥራ ለምክር ቤት ሲቀርብ አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ መቅረብ እንደሚኖርበት በመግለጽም፤ በባለሙያዎች የሰው ኃይል ፍልሰት ጉዳይ መፍትሔ ሊሰጠው እንደሚገባም አመልክተዋል።

የታራሚዎች አቅርቦት ላይ ቅሬታ ይነሳበት የነበረውን የበጀት ማስተካከያ በማድረግ ምላሽ መሰጠቱን ቋሚ ኮሚቴው በበጎነት አንስቷል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቻይና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሰጡት መግለጫ ይፋ ማድረጋቸውን አስታውሰው፤ የግንኙነት ማዕቀፍ ማደጉ የመጀመሪያው ስኬት ነው ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ በከፍተኛ ደረጃ ፖለቲካዊ የጋራ መተማመን መጠናከሩ የጉብኝቱ ሁለተኛው ውጤት ነው።

ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ ቻይና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ ደህንነትና የልማት ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ ድጋፍ ታደርጋለች ማለታቸውን አምባሳደሩ ጠቁመው፤ ሁለቱ ወገኖች አብሮነትንና ትብብርን አጠናክረው ለመቀጠል፤ አንዳቸው የሌላውን መሠረታዊ ፍላጎቶችና ዐብይ አጀንዳዎችን በሚያካትቱ ጉዳዮች ላይ መደጋገፍ የሚያስችል መተማመን ላይ መድረሳቸውንም አውስተዋል።

ትብብርን የበለጠ ማጠናከርን የሚመለከት ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ እንደ «ቤልት ኤንድ ሮድ» እና የቻይና አፍሪካ ትብብር ፎረምን በመሰሉ እንዲሁም ኢትዮጵያ ከጦርነት በኋላ የምታካሂደውን ተሃድሶ እና ኢኮኖሚያዊ መነቃቃት ለመደገፍ፤ የአረንጓዴ ልማት ትብብርን ለማጠናከርና ተግባራዊ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ጋር ለመሥራት የታየው ቁርጠኝነት ሦስተኛው የጉብኝቱ ውጤት ነው ብለዋል፡፡

አያይዘውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይና ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ኪያንግ በ «ቤልት ኤንድ ሮድ» ትብብር፣ በዓለም አቀፍ ልማት ኢኒሼቲቭ ትግበራ፣ በግብርና፣ በባህል፣ በጤና፣ በዲጂታል ኢኮኖሚ፣ በአረንጓዴ ልማት እና በከተማ እና በመሠረተ ልማት ግንባታዎች 12 የመግባቢያ ስምምነቶች እና ሁለት የፍላጎት ሰነዶች መፈራረማቸውንም አንስተዋል፡፡

አምባሳደር ዣኦ ዥዩዋን እንደተናገሩት፤ የ«ቤልት ኤንድ ሮድ» 10ኛ ዓመትን ለማክበር የቻይና መንግሥት ባሰናዳው መርሐግብር ሦስት ከፍተኛ ደረጃ የዲጂታል ኢኮኖሚ፣ የግንኙነትና የአረንጓዴ ልማት መድረኮች ተካሂደዋል።

ከ151 ሀገራት የተውጣጡ ከ10 ሺህ በላይ ተወካዮች እና 41 ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም በተሳተፉበት መድረክ፤ «የቤልት ኤንድ ሮድ» ትብብርን አስደናቂነትና ዓለምአቀፍ ተፅእኖ በድጋሚ ማሳየት ተችሏል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እ.አ.አ. ከ2019 ወዲህ ከአራት አመታት በኋላ ወደቻይና ባደረጉት ጉዞ ቤጂንግ፣ ሻንጋይና ቼንግዱ ከተሞችን ጎብኝተዋል ያሉት አምባሰደሩ፤ «ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሻንጋይና የቼንግዱ ከተሞች እድገት በጣም እንዳስደነቃቸውና ለተጨማሪ ትብብር ቡድኖችን እንደሚልኩ መናገራቸውን ገልጸዋል።

አክለውም የቻይና ኤምባሲ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የጉብኝቱን ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ በትኩረት እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

# ኢትዮጵያ በመርሆዎች መግለጫ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አስመልክቶ መግለጫ አውጥቷል።

በመርሆዎች መግለጫ ስምምነት መሠረት በሚደረግ ውይይት አዎንታዊ ውጤት ላይ መድረስ እንደሚቻል ኢትዮጵያ ታምናለች ሲል የሚኒስቴሩ መግለጫ አመላክቷል።

በዚህም መሠረት በዚህ በድርድሩ ሂደት ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ውጤት እንዲመጣ ለማስቻል ኢትዮጵያ በቅን ልቦና ትካፈላለች ሲል ሚኒስቴሩ ገልጿል።

ውይይቱ ሦስቱ ሀገራት ጠንካራ አጋርነት ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት አካል መሆኑን ያመላከተው ሚኒስቴሩ፤ በዚህ ሂደት ሀገራቱ የዓባይን ወንዝ ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ አጠቃቀም የማረጋገጥ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው ብሏል።

ሚኒስቴሩ እነዚህ ውይይቶች ሦስቱ ሀገራት የሁሉንም ፍላጎት የሚያስጠብቁ የመግባቢያ ሃሳቦችን በማፍለቅ በትብብር እንዲሠሩ ያስችላቸዋል ሲል አሳውቋል፡፡

ሀገራቱ የሁሉንም የተፋሰሱን ሀገራት ጥቅምና ስጋቶች ተረድተው በፍትሐዊ እና ምክንያታዊ ተጠቃሚነት መርህ ላይ በመመስረት ከተደራደሩ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ስምምነት ላይ እንደሚደርሱ ታምናለች ሲልም አስገንዝቧል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወደብን ጨምሮ በማንኛውም የትብብርና የልማት ጉዳይ ዙሪያ መነጋገርና መወያየት ሊበረታታ ይገባዋል!

ሰላም እና አንድነት፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ሀገራዊ ሉዓላዊነት፣ በጥቅሉም ሁለንተናዊ ብልጽግና ለአንድ ሀገርና ሕዝቦች ዘለቄታዊ ሕልውና ወሳኝ ጉዳዮች፤ ዘመኑም የሚፈልጋቸው መሠረታዊ አጀንዳዎች ናቸው:: ኢትዮጵያም እንደ ሀገር በኅብር የደመቀው አንድነቷ እንዲጸና፤ ሰላሟና ኢኮኖሚያዊ ዕድገቷ እንዲረጋገጥ፤ ሁለንተናዊ ሉዓላዊነቷ እንዲጠበቅ፤ ሁሉን አቀፍ ብልጽግናዋም እውን እንዲሆን የልጆቿ ሕልምና ምኞት ነው::

ይሄ የልጆቿ ሕልምና ምኞት ግን በሃሳብ ብቻ የሚሳካ አይሆንም:: ይልቁንም ለተግባር የቀረጠ ልብን፤ ለሥራ የማይሰንፍ ጉልበትን፤ ለፈተናዎች የማይንበረከክ ሥብዕናን፤ በሂደቱ የሚጠይቀውን ዋጋ እና መሥዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጀ ማንነትን፤... በእጅጉ ይፈልጋል:: ከዚህም በላይ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ አቅምን መለየት እና በጊዜውና በትክክለኛው አግባብ መጠቀምን ይጠይቃል::

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ትልቅ የመልማት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፣ የመልማት አቅምን ጭምር በጉያቸውና በዙሪያቸው የያዙ ሀገራት፤ የሕዝቦቻቸውን የሰላም፣ የአብሮነት፣ የልማት፣ የሉዓላዊነትና ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን እውን የማድረግ ከፍ ያለ ጥያቄ ለመመለስ ይሄንን በውስጥም በዙሪያም ያለን ሀብትና አቅም ለይቶ ለመጠቀም የሚያስችል ርዕይን መያዝ ከመሪዎች ይጠበቃል::

በኢትዮጵያም ይሄን አይነት የዜጎች ጥያቄ ለመመለስ ብቻም ሳይሆን፤ እንደ ሀገር የመቀጠልና ያለመቀጠል ህልውናዋን ለማረጋገጥ እንዲህ አይነቱን ርዕይ መጎናጸፍ በእጅጉ የሚጠይቅ ነው:: በዚህ ረገድ፣ ኢትዮጵያ የ 120 ሚሊዮን ዜጎቿን አብሮነት ማስቀጠል፤ ሰላማቸውን ማጽናት፤ የኢኮኖሚ እና የልማት ጥያቄያቸውን መመለስ፤ ሉዓላዊነታቸውን ማረጋገጥ፤ ሁለንተናዊ ብልጽግናቸውን እውን ማድረግ የዘመኑ የቤት ሥራ ነው::

ይሄን ከማድረግ አኳያም እንደ ሀገር የተጀመሩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ውጤት እያመጡ ናቸው:: ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያን ከተረጂነት ወደ ላኪነት ያሸጋገራት የስንዴ ልማት ሥራ እንደ አንድ አብነት የሚጠቀስ ነው:: በሩዝ፣ በፍራፍሬ፣ በሻይና ሌሎችም መስኮች እየተከናወኑ ያሉ የግብርናው ዘርፍ ውጤታማ ጅምሮችም የኢትዮጵያን የመልማት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን አቅምም ያሳዩ ሆነዋል::

በዚህ መልኩ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች በዲፕሎማሲው ዘርፍ ውጤቶች መታገዝ ስለሚገባቸውም፣ በዲፕሎማሲው መስክ እየተሠሩ ያሉ ተግባራትም የኢትዮጵያን ትልቅነት ብቻ ሳይሆን የቀጣይ የልማትና ዕድገት ስበት ማዕከልነትም ያረጋገጡ ናቸው:: ከሩስያ፣ ከአሜሪካ፣ ከቻይና፣ ከአውሮፓ፣ ከአፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር እያደረገች ያለው ፍሬያማ ዲፕሎማሲ በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ተመስርቶ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ብዙ ያተረፈችበት፤ እያተረፈችም ያለችበት ሆኗል::

ይሄ በውስጥ ያለ አቅምን ለይቶ የማልማትና የመጠቀም ጅምር፤ የውጭ ትብብርና ወንድማማችነትን የማጠናከር ሂደት ደግሞ ሌላ ከፍ ያለ የመልማት ጥያቄን መውለዱ አይቀሬ ነው:: ምክንያቱም፣ ማምረት ካለ ከራስ አልፎ ወደ ውጪ መላክ አለ:: ማምረት ካለ ከውጭ ግብዓቶችን ማስገባት አለ:: የበለጠ ማደግ ካለ ደግሞ ሀገራዊ ሉዓላዊነት ላይ የሚደቀኑ ፈተናዎችን ማቋቋም የሚያስችል ዘርፈ ብዙ ዝግጁነትን ማጠናከር አለ::

እነዚህ መኖሮች ደግሞ እንደ ሀገር ለብቻ የመቆም ጉዳይ አይደሉም:: ይልቁንም ከጎረቤቶች ጋር አብሮ ማደግን፤ አቅምና ሀብትን አስተሳስሮ ለተሻለ ብልጽግና መራመድን፤ ወንድማማችነት ትብብርና ትስስርን ማጠናከርን፤ በጥቅሉ ቀጣናዊ አቅምን ማደራጀትን ይጠይቃል::

ይሄ ቀጣናዊ መደርጀት ደግሞ ኢኮኖሚያዊም፣ ፖለቲካዊም፣ ዲፕሎማሲያዊም፣.. ጉዳዮችን የሚጨምር ነው:: ለዚህ ደግሞ ሰላም ያስፈልጋል፤ ለሰላም ደግሞ መነጋገር ይጠይቃል፤ መነጋገር ሲኖር ደግሞ አብሮ የመልማት ፍላጎት ያድጋል:: አብሮ ለማደግ ፍላጎት ካለ ደግሞ ሀብትን፣ ጉልበትን፣ ቴክኖሎጂን ባጠቃላይ ለሁለንተናዊ ብልጽግና የሚሆኑ አቅሞችን አስተባብሮ ለመጠቀም እድል ይሰጣል::

ኢትዮጵያም ዛሬ ላይ ሁሉ ነገር ቢኖራትም አንድ የጎደላት ነገር አለ:: በአንጻሩ ጎረቤቶቿ ሁሉ ነገር ቢኖራቸውም ሌላ የጎደላቸው ነገር ይኖራል:: ይሄ ጉድለት ደግሞ ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ፤ ጎረቤቶቿም ከእሷ ማሟላት የሚችሉበት እድልም አቅምም አለ:: ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ የወጪና የገቢ ሸቀጦችን አስተማማኝና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ የምታሳልጥበት የባህር በር (ወደብ) ያስፈልጋታል::

ይሄን የባህር በር ስትሻ ደግሞ እንዲሁ ከመሬት ተነስታ አይደለም:: የ 120 ሚሊዮን ሕዝብን የመልማትና የደኅንነት ጥያቄ ለመመለስ እንጂ:: ይሄን የሕዝቦቿን የመልማትና የደኅንነት ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ የጎረቤቶቿን ወዳጅነት፤ የቀጣናውን አብሮ የመልማትና ለዚህ አቅም የሚሆኗቸውን ሀብቶች በጋራ አልምቶ የመጠቀም መርህን ታላሚ በማድረግ ነው::

ምክንያቱም ወቅቱ ሰላምን፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን፣ ሀገራዊም ሆነ ቀጣናዊ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ በጋራ መሥራትን የሚጠይቅ ነው:: ይሄ በጋራ መሥራት ደግሞ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል አቅም እና ሀብትን ከመለየት ይጀምራል:: እንዴት በጋራ አልምቶ በጋራ መጠቀም እንደሚቻል ቁጭ ብሎ መምከርና መግባባት ላይ መድረስን ይጠይቃል:: ይሄ የሚሆነው ግን በጋራ መሥራትና በጋራ መልማት ያለውን ፋይዳ መገንዘብ ሲቻል ነው::

ኢትዮጵያም 'ሁሉ ኖሮኝ በወደብ (የባህር በር) ችግር ምክንያት የዜጎቼን የመልማትም፣ የአንድነትና ሉዓላዊነትም ጥያቄዎች በዘላቂነት ለመመለስ የማልችልበት ደረጃ ላይ እየደረስኩ ነው፤ ስለዚህ ያለኝን አካፍዬ ያላችሁን ተካፍዬ በጋራ መልማትም፣ መበልጸግም እንድንችል እንነጋገር እና የባህር በር ላግኝ'፤ ብላ መጠየቋ ከኢትዮጵያ ግላዊ ጥቅም አኳያ የሚገለጽ አይደለም::

ይልቁንም ቀጣናዊ አቅሞችን አስተባብሮ የመጠቀም፤ ሀብትን በጋራ የማልማትና ሁሉን አቀፍ የጋራ ብልጽግናን እውን ማድረግ የመቻልን እውነታ በመረዳት እንጂ:: በመሆኑም የኢትዮጵያ የወደብ ፍላጎት ሃሳብና ጥያቄ ለቀጣናዊ ልማትንም፣ ለፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነትም እድልና መንገድ መሆኑን መገንዘብ የተገባ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## **ኢትዮጵያ** ሆይ ማእድሽ ሙሉ ይሁን! ሰላምሽም ይብዛ፤

**በግርማቸው ጋሻው**

### የጉዞ ማስታወሻ

እለተ ረቡዕ መስከረም 16/2016- የመስቀል ደመራ የሚበራበት ቀን ነበር:: በመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስቴር የሚመራውና ከ 11 የሚዲያ ተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎችን የያዘውን ቡድን ለመቀላቀል ከመኝታዬ የተነሳሁት ማልጄ ነበር:: የጉዞው መዳረሻው የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ሲሆን ዓላማው ደግሞ በክልሉ እየተከናወኑ ፣ በመንግሥትና በባለሀብቶች እየተከናወኑና በመከናወን ላይ የሚገኙ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እንዲሁም እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጎብኘት፤ የተለያዩ ዘገባዎችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ማሳወቅ ነበር::

የመኪናው የጉዞው መስመር መኖሪያ ሰፈሬን ወይም ዘነበወርቅን አቋርጦ የሚያልፍ በመሆኑ ወደ ጉዞ መነሻው ወይም የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ መሄድ ሳያስፈልገኝ እዛው በሰፈሬ ቆሜ የመኪኖቹን መምጣት መጠባበቅ ጀመርኩ:: የጉራጌና የደቡብ ልጆች ሻንጣዎቻቸውን በተለያዩ እቃዎች እስከአፍጢማቸው ሞልተው ፤ ወዳጅ ዘመድ ለመጠየቅም ሆነ በዓልን ከቤተሰብ ጋራ ለማሳለፍ ፤ ብቻ ወደ ሀገር ቤት እያቀኑ ነበር::

ወጪ ወራጁን፤ አላፊ አግዳሚውን ስመለከት የእጅ ስልኬ አቃጨለ:: አጋፔ ግዮን የመሥሪያ ቤታቸችን የካሜራ ባለሙያ መሆንዋን ከእጅ ስልኬ ተገንዝቤያለሁ:: "ከፊት የምታየው ኮስትር መኪና ውስጥ ግባ" አለችኝ:: ወደ መኪናው ገብቼ ግራ ቀኙን ሳማትር፤ ሁሉም የሚዲያ ባለሙያዎች፤ ፈንግል እንደመታቸው ዶሮዎች ወዲህና ወዲያ ፍንግል.... ፍንግል ብለዋል:: በእርግጥ ሁሉም ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ እንቅልፍ እንዳይጥላቸው በአንድ ዓይናቸው ተኝተው በሌላ ዓይናችው መንጋቱን ሲጠባበቁ ማደራቸውን መገመት ከባድ አይሆንም:: ጨለማው ለንጋት ቦታውን እየለቀቀ ሲመጣ ፤ የተኛው ሁሉ ተነቃቃ:: ለወትሮው ፉልና ሌሎች ፈጣን ምግቦችን መመገብ የለመደው የጋዜጠኞች ቡድን ፤ አፉን በኬክና በውሃ እያሟሸም ከመጓዝ የተሻለ አማራጭ አልነበረውም:: መኪናዋ የጅማን የጉዞ መስመር ይዛ ትነጉዳለች::

ሰማዩ ጠቁሯል:: ከሰማይ እስከ ምድር የተለቀቀና አቅም የሌለው መጋረጃ የሚመስለው ጉም አልፎ አልፎ የሚታይ አስደማሚ ክስተት ነበር:: ተፍኪ የምትባለው መለስተኛ የገጠር ከተማ ደርሰናል:: በአስፋልቱ ግራና ቀኝ የሚገኘው ስፍራ በርከት ያለ ውሃ አዝሏል:: ውሃውን ለሁለት የሚከፍለው አስፋልት ፤ ስፍራውን ሬንጅ የፈሰሰበት በረዶ አስመስሎታል:: በመኪናው በስተቀኝ በኩል ለአበባ አልሚ ባለሀብቶች ተሰጥቶ የነበረና አሁን ላይ ምንም አይነት አገልግሎት የማይሰጥ መጠነ ሰፊ ሄክታር ላይ ዓይኔ አረፈ:: የድንኳን ማቆሚያው ብረት ሲቀር፤ የላስቲክ ድንኳኖቹ በጊዜ ብዛት ከጥቅም ውጪ ሆነዋል:: ቦታው ለምንም ዓይነት አገልግሎት ላለመዋሉ ምስክሩ፤ አደይ አበባ በቅሎበት መታየቱ ነው ::

ሰዓቱ እየገፋ ሲመጣ፤ እኛም ወደፊት እየቀዘፍን፤ ግቤ በረሃ ላይ ደረስን :: ይህን ጊዜ የፎቶን የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያዎች በቀኝና በግራ መስኮቶች በኩል የሚታየውን ውብ ተፈጥሮ በምስል ለማስቀረት መራወጥ ጀመሩ:: ሌሎቻችንም የእጅ ስልካችንን ተጠቅመን በግብር መሰልናቸው:: ግቤ በረሃ በቀደመው ግርማ ሞገሱ እንዳለ አለ:: አንዳንድ ቦታ ላይ በአስፋልት ጥገና ምክንያት የመንገድ ለውጥ ለማድረግ ከመገደዳችን በቀር ጉዞው ቀና፤ እኛም ዘና ብለናል:: በድንቅ የተፈጥሮ ውበት እየተደመምን፤ የግቤ ወንዝን ማቋረጥና ምሳን መዝለል አንድና ያው ናቸው በሚለው ተስማምተን ፤ ከአድካሚ ጉዞ፤

**የፍቅር ከተማ ተብላ የምትጠራው ጅማም እንደሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በእለቱ የደመራና የመውሊድ በዓላትን በድምቀት አክብራለች**

ድካምና ረሃብም በኋላ ከቀኑ ዘጠኝ ተኩል ሲል ጅማ ከተማ ደረስን::

የምሳ ሰዓት አልፎም ቢሆን ሁሉም ተጓዥ ረሃቡን ለማስታገስ በእውር ድንብር የተገኘውን ለመቅመስ ከመኪናው ወረደ:: የፍቅር ከተማ ተብላ የምትጠራው ጅማም እንደሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በእለቱ የደመራና የመውሊድ በዓላትን በድምቀት አክብራለች:: የየትኛውም የሃይማኖት ተከታይ ልትሆን ችላለህ፤ በጅማ ስትኖር ሃይማኖት፤ ማህበራዊ መስተጋብርና ፍቅርን ለማጠናከር ምክንያት እንጂ ለልዩነት ስጋት ሆኖ አይውቅም ይላሉ ለምሳ ካረፍኩበት ሆቴል በጋራ ምግብ እየበሉ የነበሩ ወጣቶች:: ያስምርላችሁ ከማለት ውጪ ምን ይባላል::

አመሻሹ ላይ የጅማ ቆይታችንን አጠናቀን ወደ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

# ኢትዮጵያ ሆይ ማእድሽ ሙሉ...

ከገጽ 5 የዞረ

አመያ አቀናን፡፡ ከጅማ ወደ አመያ የሚወስደው መንገድ በኮስትር መኪና የማይሞከር ነው፡፡ መንገዱ በግንባታ ላይ እንደሆነ የሚያሳብቁ ነገሮች ቢኖሩም፤ የመንገድ ሥራው መዘግየቱ ብዙ ዋጋ እንዳስከፈለ አላፊ አግዳሚው የሚያረጋግጠው እውነት ነው፡፡ ወዲህ ድቅድቅ ጨለማ፤ ወዲያ ጥቅጥቅ ያለ ደን ጉዞውን አስፈሪና ከአሁን አሁን ምን ሊከሰት እንደሚችል ማንም መገመት እንዳይችል አደረገው፡፡ በፍርሃት ተውጠው የሚቁለጨለጩ ዓይኖች በመኪናው የፊት መብራት እየታገዙ አንዳንዴም ወደላይ ከፍ እንደገና ወደታች ዘጭ ማለት ብቻ ሣይሆን በርከት ያለ አቧራ መቃም፤ የአስቸጋሪው የሌሊት ጉዞ መገለጫዎች ነበሩ::

ከሌሊቱ አራት ሰዓት ሲሆን በጉዟችን መሃል አንድ አስደንጋጭ ክስተት ተፈጠረ:: መኪናዋ ከወደ ኋሏዋ የተለየ ድምጽ ማሰማት ጀመረች:: ቀድሞም የመንገዱን አስቸጋሪነት የተረዳውና ሲማረር የነበረው ሹፌር ፊቱ ተለዋወጠ:: ድንጋጤው አስደነገጠን:: መኪናው የመንገዱን ዳር ይዞ ቆመ:: ሁሉም ነገር ጨለማ ሆነ:: ሁላችንም ጸጥ ረጭ አልን:: ከነፍሳት ሲርሲርታ በቀር የሚሰማ ነገር የለም:: ሹፌሩ ድቅድቁን ጨለማ በመጠኑም ቢሆን በባትሪ አብርቶ፤ በመኪናው የኋለኛ እግር አካባቢ የተፈጠረውን ነገር አጤነ::

ሹፌሩ ወደ ውስጠኛው የመኪና ክፍል ሲገባ ሁሉም የሆነው ለማወቅ "ምንድነው?" በአንድነት ጠየቅን:: "የመኪናው ባሌስትራ ተሰብሯል" አለ የለበሰው ልብስ በሚያካፋው ዝናብ የረሰረሰው ሹፌር መለሰ:: የመኪናውን በር ዘግተን ከኋላችን ሲጓዝ ነበረውን መኪና መጠበቅ የግድ ሆነብን:: ከአፍታ ቆይታ በኋላ፤ ሲጠበቅ የነበረው መኪና ደረሰ:: ሌላኛው ሹፌር የሆነውን ክስተት በቅጡ ከተረዳ በኋላ፤ ወደ እኔ መኪና ሂዱ፤ የተበላሸው መኪና ቀስ ብሎ ይምጣ አለ እኛም በሃሳቡ ተስማምተን እቃዎቻችንን ይዘን ጉዞ ቀጠልን ::

በእንቅልፍም በንቃትም ብዙ ከተጓዝን በኋላ አመያ ወደተሰኘች አነስተኛ የገጠር ከተማ ደረስን:: መምጣታችንን ሲጠባበቅ የነበረው የአመያ ህዝብ አቀባበሉ ልዩ ነበር:: የእራት ብሉ ግብዣ የቀረበልን፤ እንደደረስን ወይም ለእኩለ ሌሊት ተኩል ሰዓት ሲቀረውም ቢሆን ትንሽ ለመቀማመስ አልቦዘንም:: አኩራፊ ሰው ምሳው እራቱ ይሉለታል እንዲል ተረቱ:: በጉዞው መጎሳቆላቸው ያሰቡ አንዳንዶች ዓይናችን ለመኝታ እንጂ ለምግብ አይገለጥም ብለው ጠማቸውን አደሩ:: የሆነው ሆኖ ከአስራ ስምንት ሰዓታት ጉዞ በኋላ አዳራችን በዚያው ሆነ:: ተኝቶ እንደ መነሳት ያለ አእምሮን የሚያድስ ነገር ምን አለ:: በብዙ ድካም የዛለው ስጋችን አሁን እረፍት አገኘ::

መሸቶ መንጋቱ አይቀርምና ነጋ:: ከወደቅንበት አልጋ ዓይናችንን እንድንገልጥና እንድንነቃ ምክንያት የሆኑን የመንደሩ ህፃናት ነበሩ:: እነሱ ፤መስቀልን በዓመት አንድ ጊዜ የሚያገኙት በዓል ስለሆነ ልዩ ቦታ ይሰጡታል:: አስር የሚሆኑ ህጻናት በቅደም ተከተል ተሰልፈውና ድምጻቸው ከፍ አድርገው በኮንታ ብሔር ቋንቋ ሂዮ..... ሂዮ በዓለ... ሂዮ እያሉ ደጋግመው ይዘፍናሉ:: እንኳን አደረሳችሁ፤ እንኳን አደረሰን እንደ ማለት ነው:: ይህን በየሰዉ ደጃፍም እየቆሙ ደጋግመው ያዜሙታል:: በምላሹም፤ ትንሽ ሳንቲም የሚሰጣቸው አለ:: ሌላው ደግሞ ወደ ቤት እንዲገቡ ያደርግና ቤት ያፈራውን ይጋብዛቸዋል:: እነሱም ለዓመት ያድርሰን እያሉ አመስግነው ወደ ሌላው መንደር ይሄዳሉ::

> ከበዓሉ አከባበር ጋር ተያይዞ እርድ የሚከናወነው በታዋቂ ሰዎች ደጃፍ ላይ ነው:: የስጋ ክፍፍል በሚከናወንበት ጊዜም የድሃ ድሃ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ በማድረግ ነው:: በበዓሉ ሁሉም ተደስቶ እንጂ አዝኖ መዋል የለበትም የሚል የጋራ እሳቤ እዛ አለ:: በእለቱ አንድ የማህበረሰቡ አባል ቡና ተጠርቶ ሲሄድ አደይ አበባ ሣይዝ ወደተጠራበት ቤት መሄድ ነውር ነው

ከበዓሉ አከባበር ጋር ተያይዞ እርድ የሚከናወነው በታዋቂ ሰዎች ደጃፍ ላይ ነው:: የስጋ ክፍፍል በሚከናወበት ጊዜም የድሃ ድሃ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ በማድረግ ነው:: በበዓሉ ሁሉም ተደስቶ እንጂ አዝኖ መዋል የለበትም የሚል የጋራ እሳቤ እዛ አለ:: በእለቱ አንድ የማህበረሰቡ አባል ቡና ተጠርቶ ሲሄድ አደይ አበባ ሣይዝ ወደተጠራበት ቤት መሄድ ነውር ነው::

ሁሉም ሰው ከተጠራበት ደጃፍ ሲደርስም ሂዮ..... ሂዮ በዓለ... ሂዮ እያለ ይገባል:: እንኳን አደረሳችሁ ... እንኳን አደረሰን እንደማለት ነው:: ይህ ባህላዊ ሥርዓት ህጻን-አዋቂ ፤ ሴት-ወንድ ሳልለይ በሁሉም የብሄረሰቡ ተወላጅ የሚከወን ነው:: ከዚያም ቤት ያፈረራውን ምግብም ሆነ መጠጥ ከዘመድ፤ ወዳጅና ጎረቤት ጋር በመሆን ከአንዱ ቤት ወደ ሌለው እየተጠራሩ እየበሉና እየጠጡ በዓሉን በጋራ ከመስከረም 1 እስከ 30 ያከብራል:: ሲሊሶ፤ ሱልሶ፤ ኡስታ፤ ባጭራ፤ ኩቶኩብዋ እና ሌሎችም ምግቦች የበዓሉ መድመቂያ ናቸው:: ኩላኩሎ፤ ቦርዴ እና የመሳሰሉት መጠጦችም በዓሉን ያሳምሩታል::

የአመያ ቆይታችንን አጠናቀን ወደ ኮይሻ ተንደረደርን:: በጉዞአችንም ስለ አዳራችን ፤ ስለውሎአችን፤ በአካባቢው ስለሚታየው ድንቅ ተፈጥሮ፤ እዚህም እዚያም ከጫካ ብቅ ብለው ወዲያው ጥልቅ ስለሚሉት የዱር እንስሳት ተፈጥሮ፤ ቀልድም ቁምነገርም እያነሳንና እያወጋን የቀረንን 13 ኪሎሜትር አገባደን ኮይሻ ገባን:: ይህችን አነስተኛ የገጠር ከተማ በሰው ብዛት ደመቅ ያለች ብትሆንም እርጅና የተጫናት ትመስላለች:: ለዚህች ከተማ ህልውናዋ የንጹህ ማርና ቅቤ እንዲሁም ፍራፍሬዎች መገበያያ ማእከል መሆኑዋ ነው:: በዚያ የሚያልፍና ለቦታው እንግዳ የሆነ ሰው ሁሉ ማር ይዞ ለመሄድ መቋመጡ አይቀሬ ነው:: እኛም፤ ስንመለስ እንደርሳለን በሚል አንድ ሃሳብ ተስማምተን መንገዳችንን ቀጠልን::

ኮይሻ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ እንደደረስን ምልክቱ፤ ከፊታችን የታጠረ ኬላ መገኘቱ ነው :: ከኬላው ለማለፍ የፈቃድ ደብዳቤ ማሳየት ብቻውን አይበቃም:: በእጅ የተያዘ ሻንጣም፤ ላፕቶፕና ካሜራ ማስፈተሽና ማስመዝገብ የግድ ነው:: የተጠየቀውን መስፈርት ሁሉ ካሟላን በኋላ እንድንገባ ተፈቀደልን:: በፕሮጀክቱ የጥበቃ ሠራተኞች እየተመራን ወደተዘጋጀልን ማረፊያ አመራን::

የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቱ አጠገብ ተራራማ ቦታ ላይ ደረጃቸውን ጠብቀው የታነጹ የሠራተኛ መኝታ ክፍሎች ይታያሉ:: አሠራራቸው ከመለስተኛ ደረጃ ሆቴል ቢበልጡ እንጂ አያንሱም:: ከ ቪ.አይ.ፒ እስከ ተራ ሠራተኛ ድረስ ወደ ፕሮጀክቱ ለሚመጡ እንግዶች፤ ነጻ የመኝታ አገልግሎት ያቀርባል:: እኛም ለእንግዳ ማረፊያ ተብለው የተሰናዱትን ክፍሎች ቁልፍ ተረከብን:: ሻንጣዎቻችንን ከመኪናው አወረድንና ከሻወር በኋላ ወደ ምሳ ለመሄድ ተቀጣጥረን በየክፍላችን ገባን::

እያንዳንዱ ማረፊያ ክፍል፤ ሻወር፤ ሽንት ቤትና የመኝታ ክፍሎች አሉት:: ከሻወር በኋላ ወደ ምግብ አዳራሹ አመራን:: እኛ ካረፍንበት መኝታ ክፍል አዳራሾቹ ጋር ለመድረስ ከ 2-5 ደቂቃ ይፈጃል:: በቅርብ ወዳገኘነው አዳራሽ ስንገባ የፕሮጀክቱ ሠራተኞች ምሳቸውን እያጣደፉት ነበር:: የምናውቀው ሰውን ፍለጋ አዳራሹን ከጥግ ጥግ አማተርን፤ ነገር ግን ሁሉም ፊት ለኛ አዲስ ነበር:: ግራ መጋባታችንን እንግዳ መሆናችንን የተረዱ አንዳንድ ሠራተኞች ወደ ሌላኛው አዳራሽ እንድንጓዝ አመለከቱንና ወደዛው አመራን:: በጎጆ ቤት ቅርጽ ከተራራ ጫፍ ላይ ዘመናዊ ሆኖ የተገነባው ሌላኛው የምግብ አዳራሽ በዙሪያው ያለውን ውብና ማራኪ ሰንሰለታማ ተራሮች ፍንትው አድርጎ ያሳያል:: አረንጓዴ ምንጣፍ የለበሱ የሚመስሉት እነዚህ ተራሮች ጥቅጥቅ ባለ ደን ተሸፍነዋል::

ሰንሰለታማ ተራሮቹን ልዩ ውበት ያጎናጸፈቸው ደግሞ ከግርጌያቸው የሚገኙት ሜዳማ ቦታዎች ናቸው:: ይህን በዓይን ተመልክተው የሚጠግቡት አይደለምና በሞባይል ስልካችንም በካሜራዎቻችንም ውበቱን አስቀረነው:: የተገኘውን ቀማምሰን እንደጨረስን፤ የሥራ መመሪያም ተቀበለን:: ከድካም በጸዳ አዲስ መንፈስ ሆነን የግድቡን ሥራ አፈጻጸም ማየቱ ስለታመነበት ተረፈ መዓልቱን ወደ ክፍሎቻችን ሄደን እረፍት አደረግን::

በበነጋው ጠዋት ላይ ተነሳንና የተዘጋጀልንን ሆቴል የሚያስንቅ ቁርስ ተመገብን:: ቀጣዩ የጉዟችን መዳረሻ የኮይሻ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ ነበርና ወደዛው አመራን:: ቀድሞ የመጣንባቸው ኮስተር ሚኒባሶች ወደ ግድቡ የሚያወርደውን ጠመዝማዛና ቁልቁለት መንገድ ለመሄድ ስለማይችሉ እዛው ባሉበት እንዲቆዩ ተፈረደባቸው:: ለዚህ መንገድ ተመራጭ የሆኑ ትንንሽ መኪኖች ውስጥ ገብተን፤ ትንሽ እንደተጓዝን አንድ ማማ ላይ ደረስን:: እዚህ ማማ ላይ ቆመህ ሁሉንም የግድቡን ሥራዎች ያለከልካይ ማየት ትችላለህ::

እጅግ በርካታ ሠራተኞች ግድቡን እውን ለማድረግ ቀንና ሌት፤ ለ 24 ሰአታት ያለማቋረጥ ይተጋሉ:: ለቃለ ምልልስ በቆምንባቸው ጥቂት ደቂቃዎች፤ ላብ ጀርባችን ላይ ይንዠቀዠቅ ያዘ:: ምላሳችንም እንደኩበት ደረቀ:: እኛ እንዲህ ከሆን፤ ሌት ተቀን የሚታትሩት ሠራተኞች ሙቀቱን እንደምን ቻሉት? ለሚለው የህሊና ጥያቄዬ መልስ አጣሁለት :: ወጣት ሴት እንጂነሮች ከወንድ የሙያ አጋሮቻቸው ጋር ሆነው ይወጣሉ ይወርዳሉ:: እንደገና ከማማው የሚያሰወርዱትን ጥቂት መንገዶችን ቁልቁል ወረድን:: የግድቡ የሲቪልና የመካኒካል ሥራዎች የሚከናወኑበት ቦታ ላይ ሆነን ሁሉን በቅርበት ተመለከትን:: የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቱ እራትም መብራትም ለመሆን ግስጋሴውን አጠናክሮ ቀጥሏል::

ግድቡ ለኢትዮጵያውያን የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማእከልም ሆኖ እያገለገለ ይገኛል:: ፕሮጀክቱ፤ አሁን ላይ ቁጥራቸው 5000 ለሚደርሱ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል ፈጥሯል:: እነዚህ ሠራተኞች እውቀትና ልምዳቸውን እንዲያሳድጉ ብቻ ሳይሆን የሥራና የደመወዝ እድገት እንዲያገኙም ምክንያት ሆኗል ፕሮጀክቱ:: ብዙዎች ከዝቅተኛ የሥራ ደረጃ ተነስተው የትልቅ ሙያ ባለቤት ለመሆናቸው ቋሚ ምስክሮች ናቸው:: ይህ አይነቱ የአቅም ግንባታ ሥራ ሀገሪቱ ወደፊት በራስዋ አቅም መሰል ፕሮጀክቶች እንድትገነባ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ መገመት አያዳግትም::

የኮይሻ ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ ሥራው 61 በመቶ የደረሰ ሲሆን ከሶስት ወይም አራት ዓመት በኋላ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ፤ 1800 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል በማመንጨት ወደ ሀገሪቱ የሃይል ቋት እንደሚያስገባም ከጉብኝቱ ተገንዝበናል:: ለሥራችን ይጠቅመናል ያልነውን መረጃ ሰብስበን ወደ ማረፊያ ክፍሎቻችን የሽምጥ ጋለብን:: ቃለምልልሶችን ለመስራት በሚዲያ ባለሙያዎች መካከል የነበረው የሥራ ክፍፍልና ትብብ ሥራዎቻችን በጊዜ እንድናጠናቀቅ ያስቻለ ድንቅ ዘዴ ነበር:: ዜናዎቻችንን ወደ ሚዲያ ተቋሞቻችን ከላክን በኋላ ለእራት ወደ ምግብ አዳራሾች ተጓዝን:: የምግብ ጠረጴዛው በኮንታ ብሔር ባህላዊ ምግቦች የተሞላ ነበር:: ቅቤ የጠጣውን ምግብ አጣጣምነው:: ግብዣው ቀ---ጥ---ሏ---ል:: ኢትዮጵያ ሆይ ማእድሽ ሙሉ ይሁን! ሰላምሽም ይብዛ! አሜን::


ውድ አንባቢያን በክፍል ሁለት የጉዞ ማስታወሻዬ ደግሞ በጨበራ ጩርጩራ እና ሃላላ ኬላ መስህቦች ያደረግነውን ምርጥ ውሎ አስቃኛችኋለሁ:: ቸር እንሰንብት::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ምርትን ከብክነት የሚታደገው የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የህብረተሰቡን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ አዳዲስ፣ ችግር ፈቺና እሴት የሚጨምሩ ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር ረገድ በርካታ ሥራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ:: በየዓመቱ በርካታ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የፈጠራ ውጤቶች በሰልጣኞችና በአሰልጣኞች አማካይነት ተፈጥረው እየተጎበኙ፣ አልፎም ተርፎ የፈጠራ ውጤቶቹን ለሚያስፋፉ አካላት እየተላለፉ ያለበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል::

የፈጠራ ውጤቶችን ከሰሩት መካከልም የድሬዳዋ ሻሎም ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ አሰልጣኝና የወርክሾፐ ኃላፊ አቶ ሙሉቀን ሽፈራው ይገኙበታል፤ እሳቸው የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን ነው ያሰሩት:: አቶ ሙሉቀን እንደሚሉት፤ የህብረተሰቡን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ በርካታ የፈጠራ ሥራዎች ተሰርተዋል:: ከእነዚህ ውስጥ በእሳቸው የተሰራው በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው በ3ኛው የክህሎት ውድድር ላይ የቀረበው በሰው ኃይል የሚሰራ የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን አንዱ ነው::

ይህ የፈጠራ ሥራ ምንም ዓይነት ኃይል (የኤሌክትሪክ ኃይል ወይም ነዳጅ) አይጠቀምም:: ይህም ከውጭ ሀገራት ከሚገባው የበቆሎ መፈልፈያ ለየት ያደርገዋል:: ከውጭ በውድ ዋጋ የሚገባው የበቆሎ መፈልፈያ በኤሌክትሪክ ኃይል ወይም በነዳጅ አልያም ከሁለቱ በአንዱ አማራጭ የሚሰራ ነው:: አዲሱ የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን ግን በሰው ኃይል ብቻ የሚሰራ ስለሆነ ለኤሌክትሪክ ኃይል ወይም ለነዳጅ የሚወጣውን ወጪ የሚያስቀር ነው::

ይህንን የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን ለመስራት ያነሳሳቸው ዋነኛ ምክንያት በቆሎ በሀገራችን በስፋት መመረቱ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ሙሉቀን፤ በተለይ በምስራቁ የሀገራችን አካባቢ ከሁሉም የአዝዕርት ዓይነት በላይ በስፋት የሚመረት እና አመራረቱም ባህላዊ መንገድ የሚከናወን በመሆኑ እንደሆነ ይናገራሉ:: የበቆሎ ምርት በስፋት ይመረት እንጂ በሚመረተው ልክ ምርቱን መሰብሰብ እንዳልተቻለም ይጠቁማሉ:: አርሶ አደሩ ምርቱን ለመሰብሰብ የሚጠቀመው በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት በባህላዊ መንገድ ስለሆነ ምርቱ በአግባብ ለመሰብሰብ እንደሚቸገር ጠቅሰው፤ በዚህ ሂደትም ከ20 እስከ 30 በመቶ የሚሆነው የበቆሎ ምርት ለብክነት እንደሚዳረግ ይናገራሉ:: ይህ ደግሞ በአካባቢያቸው የሚመለከቱት በምርት አሰባሰብ ሂደት የሚፈጠረውን የምርት ብክነት እና የአርሶ አደሩ ችግር ለመቅረፍ በማሰብ ችግር ፈቺ ፈጠራ ለመስራት መነሳሳታቸውን ይገልጻሉ::

አዲሱ የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን የበቆሎ ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት የሚባክነውን ምርት ለማስቀረት የሚያስችል ነው:: ከዚህ በተጨማሪም በባህላዊ መንገድ ለማምረት የሚያስፈልገው ብዛት ያለው የሰው ኃይል እና የሚወስደውን ጊዜ በመቆጠብ በተሻለ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርትን የሚያመርት ጉልበትን የሚቆጥብ ማንም ሰው በቀላሉ ሊሰራ የሚችለውን የፈጠራ ሥራ መሆኑን አስረድተዋል::

ይህ ማሽን የተሰራው በአካባቢው ላይ በቀላሉ ከሚገኙ ብረት ነክ ቁሳቁስ እንደሆነ ይናገራሉ:: ማሽኑ በሰው ኃይል በማሽከርከር የሚሰራ ሲሆን፤ በሰዓት የሚያመርተው መጠን እንደሚያሽከረክረው ሰው ፍጥነት ይለያያል:: በፍጥነት የሚያሽከርክረው ሰው በሰዓት ውስጥ ብዙ ያመርታል፤ ፍጥነቱን ቀነስ አድርጎ በመጠኑ የሚያሽከረክር ከሆነ ደግሞ የሚያመርተው በዚያው ልክ ይሆናል:: የማምረት ሂደቱ እንደየሰዎቹ የማሽከርከር አቅም የሚወሰን ቢሆንም፤ አንድ መካከለኛ አሽከርካሪ ነው ተብሎ የሚገመት ሰው እንኳን ከአንድ ደቂቃ እስከ አምስት ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ እስከ 20 ኪሎ ግራም በቆሎ በመፈልፈል ማምረት እንደሚችል ይገልጻሉ:: በተመሳሳይ ፈጣን የሆነ አሽከርካሪ ከሆነ ደግሞ በደቂቃ እስከ 20 ኪሎ ግራም ማምረት የሚቻልበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመው፤ አመራረቱ እንደየሰው አጠቃቀም የሚለያየ መሆኑን አብራርተዋል::

አቶ ሙሉቀን እንደሚሉት፤ በቆሎውን ወደ ማሽኑ ለማስገባት የሰው ኃይል ሳያስፈልግ ማሽኑ በተቀመጠለት የስበት ኃይል አማካኝነት ወደ መፈልፈያው እንዲገባ ይደረጋል:: በቆሎ ወደ ውስጥ ከገባ በኋላ ሲሽከረከር በማሽት ፍሬውን ከቆረቆንዳው ላይ ያላቅቃል፤ ከዚያም በኋላ ፍሬው በአንድ በኩል፣ ቆረቆንዳው ደግሞ በሌላኛው በኩል ይወጣል:: በዚህ አመራረት ሂደት ምንም አይነት የምርት ብክነት የለም:: ቆረቆንዳውም ቢሆን ለከብቶች መኖ ሊውል የሚችል ነው:: በተለይ ለወተት ተዋጽኦ ምርት እንስሳት ዋንኛ የመኖ ግብዓት ስለሚሆን አካባቢን አይበክልም፤ ምንም የሚጣል ነገር የለም:: በፍጥነት ብዙ ምርትን በመስጠት ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ይቆጥባል::

ከውጭ የሚገባውን መተካት የሚችል በመሆኑ የውጭ ምንዛሪን በማስቀረት ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው የሚሉት አቶ ሙሉቀን፤ ማሽኑ በብዛትና በጥራት ተመርቶ አርሶ አደሩ ጋር ተደራሽ እንደሆነ ይናገራሉ::

ይህ የፈጠራ ሥራ ለሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተደራሽ ከሆነ በኋላ የውስጥ ፍጆታ ከመሸፈን ባለፈ ወደውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪን ሊያስገኝ የሚችል እንደሆነ አመላክተዋል:: ‹‹ይህ ማሽን ሲታይ ቀላል እንደሆነ ይታሰባል እንጂ በተለይ በአብዛኛው በግብርና ሥራ የሚተዳደር ሕዝብ ባላት የእኛ ሀገር አስፈላጊነቱ በእጅጉ የላቀ ነው›› የሚሉት አቶ ሙሉቀን፤ አርሶ አደሩ ከባህላዊ የአመራረት ዘዴ ወጥቶ ይህ ማሽን ቢኖረው ወይም ደግሞ ሁለት ሦስት ሆነው በሕብረት ገዝተው ቢያመርት በብዙ መልኩ ውጤታማ መሆን ይችላሉ ይላሉ:: ይህ ሲባል ደግሞ ለአርሶ አደሩ ድካም የሚያስቀር በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን ከሀገር አንጻር ያለው ጠቀሜታ ጉልህ እንደሆነ ይናገራሉ::

የበቆሎ መፈልፈያ ማሽኑ በድሬዳዋና አካባቢዋ በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ተደርጎ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል የሚሉት አሰልጣኙ፤ ማሽኑን የገዙ አርሶ አደሮችን ለራሳቸው ከመጠቀም ባለፈ ለሌሎች እያከራዩ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል ይላሉ:: ማሽኑ ተነቃቃይና ተገጣጣሚ ስለሆነ ካለበት ቦታ ላይ አንቀሳቅሶ የትም ቦታ ላይ ወስዶ መጠቀም እንደሚቻል ይናገራል:: አርሶ አደሩ ለሌላው ለማዋስም ሆነ ለማከራየት በሚፈልግበት ወቅት ነቃቅሎ በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለማዘዋዋር እንደሚችል ይገልጻሉ::

አሰልጣኙ እንደሚሉት፤ ማሽኑ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ስለማሽኑ አጠቃላይ ሁኔታ አስመልክቶ ከተጠቃሚ አርሶ አደሮች መረጃዎች መሰብሰብ ችሏል:: ቀደም ሲል በነበረው ተሞክሮ አንድ ፈጠራ ተሰርቶ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ስለ ፈጠራ ሥራው መረጃ ይሰበሰባል:: ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ከአርሶ አደሩ ግብዓቶችን በመሰብሰብ እንዲሻሻል ይደረጋል:: ከዚያ መሻሻል ያለበት ነገር ካለ እንዲሻሻል ይደረጋል:: በዚህም መሠረት ቀደም ሲል ይህንን መሰል በተወሰነ መልኩ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠራ የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን ተሰርቶ ነበር:: ነገር ግን ተጠቃሚው አርሶ አደሩ በሰጠው አስተያየት ሙሉ ለሙሉ በማንዋል በሰው እጅ የሚሰራ እንዲሆን ተደርጓል:: በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራው ከማንዋሉ አንጻር ሲታይ በጥሩ ሁኔታ ይፈለፍላል፤ ጥሩ ምርት ያመርታል፤ ፍጥነትም አለው:: ነገር ግን በሚጠዝበት ጊዜ በቆሎውን የሚሰባብርበት ሁኔታ ስላለ የተሰባበር የበቆሎ ፍሬ ደግሞ ለዘር ስለማይሆን ያ ቀርቶ በዚኛው ማሽን እንዲተካ ሆኗል::

‹‹አርሶ አደሩ ከምርቱ ላይ ለሚቀጥለው ጊዜ የሚሆነው ዘር ማስቀረት ስለሚፈልግ ይህንን ማሽን በጣም ወዶት ይጠቀምበታል›› የሚሉት አሰልጣኙ፤ በአዲሱ ማሽን የሚመረተው ምርት ለዘርም ሆነ ለገበያ፣ ለምግብ ፍጆታ ለሚፈልገው አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስችለው እንደሆነ ይናገራሉ::

ይህ የፈጠራ ሥራ በቅርብ ጊዜ የተሰራ እንደመሆኑ መጠን በድሬዳዋ አካባቢዎች ላሉ አርሶ አደሮች እና በሌሎች የተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ተደራሽ ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ነው:: ማሽኑ ቀደም ሲል ባለው የዋጋ ተመን ከ30ሺ እስከ 40 ሺ ብር ይሸጥ እንደነበር ጠቅሰው፤ አሁን ላይ የብረት ዋጋ ከመጨመሩ ጋር ተያይዞ ማሽኑን ለመሥራት የሚወጣው ወጪን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአሁኑ ጊዜ በ55ሺ ብር እንደሚሸጥ ይናገራሉ:: ‹‹ማሽኑ የሚሰራው ከጠንካራ ብረቶች ስለሆነ ቶሎ ሊበላሽ የሚችል አይደለም:: ረጅም ጊዜ የሚቆይ ነው:: ስለሆነም አርሶ አደሮች ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በአንድነት ሲገዙት ብዙ ድካም፣ ልፋትና ጊዜ የሚቆጥብ በመሆኑ በእጅጉ ጠቃሚ ነው:: አሁን ላይ ገዝተው እየተጠቀሙበት ያሉት አርሶ አደሮች እንደሚሰጡት አስተያየት ከሆነ ከዚህ ቀደም ከሰጠናቸው በቆሎ መፈልፈያ ማሽን አንጻር ይሄኛውም ማሽን እንደወደዱት የሚያሳይ ነው:: ከዚህ ባለፈ የሌሎች አዝርዕቶችን ምርት መሰብሰብ የሚያስችል የፈጠራ ሥራ ሰርተን እንድናቀርብላቸው ይጠይቃሉ›› ብለዋል::

የድሬዳዋ ሻሎም ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሟሉ ማሽነሪዎች ያሉት ሲሆን፣ የሰውን ኃይል ጨምሮ ይህን ማሽን በሀገሪቱ ለሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን አቶ ሙሉቀን ይናገራሉ:: ከድሬዳዋ አካባቢ ውጭ ያሉ አርሶ አደሮች ማሽኑን ለመግዛት ፍላጎት እንዳላቸው እየገለጹላቸው መሆናቸውን ተናግረው፣ እሳቸውም ማሽኑን እያመረቱ ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ለማዳረስ እየሰሩ እንደሚገኙም ይናገራሉ:: በቀጣይ በርከት ያሉ ማሽኖችን በማምረት ለሁሉም አካባቢዎች እንዲዳረስ ለማድረግ እቅዱ እንዳላቸው አመላክተዋል::

ከዚህ በተጨማሪም ኮሌጁ ሌሎች የግብርና ሥራን ሊያቀሉ የሚችሉ የፈጠራ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን ነው የሚናገሩት:: ለአብነትም ሲጠቅሱ የወተት መያዣ፣ ቅቤ መናጫ እና የመሳሰሉ የፈጠራ ሥራዎችን የአርሶ አደሩን ልፋትና ድካም ሊቀንሱ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመፍጠር ለአርሶ አደሩ በስፋት ተደራሽ ለማድረግ እየሰሩ እንደሚገኙ ይናገራሉ::

ይህ ማሽን ለአርሶ አደሩ ተላልፎ ዝም ብሎ የሚተው ሳይሆን፣ አርሶ አደሩ እንዴት መጠቀም እንዳለበት፤ በምን መልኩ መያዝ እንዳለበትና መሰል ማድረግ ያለበት ጉዳዮች አስመልክቶ ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርጉም ይናገራሉ:: የፈጠራ ሥራዎቹም ከተሰሩ በኋላ ጥራታቸውና ደረጃቸው በመቆጣጣሪያ መሳሪያ ተፈትሾና ተረጋግጦ እንዲሁም በባለሙያ ተጠንቶ ለአርሶ አደሩ እንደሚሰጥ ይናገራሉ:: ከአርሶ አደሩ በሚሰበሰበው ግብረ መልስ መሠረትም መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ታይተው እንዲሻሻሉ እንደሚደረግ አስረድተዋል::

አቶ ሙሉቀን እንደሚሉት፤ ማሽኑ ነዳጅ ስለማይጠቀም ምንም ዓይነት አካባቢ ሊበክል የሚችል ነገር የለውም:: የሚጣል ተረፈ ምርት የለውም ከፍሬው ጀምሮ እስከ ቆረቆንዳው ጥቅም ላይ ይውላል:: የሚያስከትለውም የጎንዮሽ ጉዳት የለም:: ለአጠቃቀም በጣም ቀላል ነው:: እስካሁን ተደራሽ ከሆነባቸው አካባቢዎች የቀረበ ቅሬታ የለም::

እንዲህ ዓይነት የፈጠራ ሥራዎች የሚሰሩት ከህብረተሰብ ችግር በመነሳት ችግሮችን ለመቅረፍ ታስቦ ነው የሚሉት አቶ ሙሉቀን፤ ይህም ሆኖ ግን የተሰሩ የፈጠራ ሥራዎችን ህብረተሰቡ አይቶና ተረድቶ አምኖባቸው እንዲጠቀምባቸው ለማድረግ ብዙ ጊዜ እንደሚፈጅ ይናገራሉ:: እስካሁን ድረስ በኮሌጁ ብዙ ዓይነት የህብረተሰቡን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ ሥራዎች ቢሰሩም ህብረተሰቡ ዘንድ ተደራሽ ሆነው እንዲጠቀምባቸው ለማድረግ ብዙ ሥራዎች እንደሚጠይቁ ጠቅሰው፤ ብዙ ዓይነት የህብረተሰቡን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ ሥራዎችን ሰርቶ ተቀባይነት ሲጠፋና በፋይናንስ የሚደግፍ አካል ሳይኖር ሲቀር ደግሞ የፈጠራውን ሥራ የሚሰራው አካል ለሌሎች ተጨማሪ የፈጠራ ሥራዎች እንዳይነሳሳ በማድረግ ወደኋላ እንዲመለስ እንደሚመለሰውም አመላክተዋል::

ህብረተሰቡ ለፈጠራ ሥራዎች ትኩረት ሰጥቶ እንዲጠቀምባቸው በማድረግ ረገድ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይጠይቃል የሚሉት አቶ ሙሉቀን፤ ችግሩን ሊቀርፉ የሚችሉ የፈጠራ ሥራዎችን ጥቅም በሚገባ ተገንዘቦ ተጠቃሚ ቢሆን ጊዜና ጉልበት በመቀነስ የሚፈለገው ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል ብለዋል:: በተለይ ይህ የፈጠራ ውጤትም ሆነ ቴክኖሎጂ በሁሉም አካባቢዎች በማስፋፋት ለህብረተሰቡ በስፋት እንዲደርስ ማድረግ እንደሚገባም አስገንዝበዋል::

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የባህር በር አማራጮችን - በቀጣናዊ ትብብሮች

**አስቴር ኤልያስ**

ኢትዮጵያ የምትገኘው ከቀይ ባህር በጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ እንደሆነ ይታወቃል:: ይሁንና ከዚህ ተፈጥሯዊ ሀብት ተጠቃሚነቷን ለማረጋገጥ አልተቻላትም:: ከዚህም የተነሳ በአፍሪካ የባህር በር ከሌላቸው 17 ሀገራት መካከል አንዷ ለመሆን ተገድዳለች::

በርግጥ ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት የራሷ የሆነ ወደብ የነበራት ሀገር ናት:: ነገር ግን ያ ሁሉ ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ የወደብ አገልግሎት ለማግኘት ስትል ጥገኛ ሆና ኖራለች:: በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በርካታ እንግልትንም አስተናግዳለች:: እንደ ራስ መሆን አይቻልምና በኢኮኖሚው ሆነ በሌላ ሌላ ጉዳይ የልቧን ለማድረግ ተስኗት ቆይታለች::

ባሳለፉቻቸው ሶስት አስር ዓመታት ውስጥ ማንም ስለ ወደብ እንዳያነሳ የተባለ ይመስል ዝም ጭጭ በመባሉ ስለ ወደብም ሆነ የባህር በር ጉዳዩ ላይከፈት የተዘጋ ይመስል ተከርችሞ መቆየቱ የሚታወቅ ነው:: በእነዚያ ዓመታት ስለ ወደብ ይገባኛል ጥያቄ ማንሳት ቀርቶ ስለጉዳዩ መነጋገርም ሆነ መወያየት እንደነውር የሚቆጠርባቸው ጊዜያት ሆነው ዘልቀዋል::

ከዚህ የተነሳ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን ወደብ አልባ እንደሆኑ በራሳቸው አሳምነው ተቀምጠዋል:: እስካለፈው መስከረም ወር ድረስም ስለ ወደብ ጉዳይም አንስቶ ለመወያየትም ሆነ አጀንዳ ለማድረግ ድፍረቱ አልነበራቸውም:: ያኛውን ወይም ይሄኛውን ወደብ በታሪካዊም ሆነ በተፈጥሯዊ መንገድ የመጠቀም መብት አለኝ በሚል ጉዳዩን ማንሳትም በራሱ የሰው እንደመቀላወጥ ሲቆጠር ከርሟል::

ከሰሞኑን ግን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት «ከጣብታ ውሃ እስከ ቀይ ባህር ውሃ» በሚል መሪ ሐሳብ ኢትዮጵያ እና ቀይ ባህር ያላቸውን ታሪካዊ ትስስርን ጨምሮ ስለወደብ ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወቃል::

በዚህ ገለጻቸው በዋናነት ሊያስርጹ የፈለጉት መልዕክት ስለ ቀይ ባህር እና ስለወደብ ጉዳይ ኢትዮጵያውያን በተለይም ደግሞ የፓርላማ አባላት አጀንዳ አድርገው እንዲወያዩበት መሆኑ እሙን ነው:: አባላቱ፣ ከተያዙበት የፍርሃት ቆፈን ተላቅቀው በባህር በር ጉዳይ መነጋገር እንዲሁም አማራጭ ሃሳቦች ላይ መምከር ተገቢነቱን አስረድተዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ የኢትዮጵያ ሕልውና እና ልዕልና የተሳሰረው ከቀይ ባህር ጋር ነው ሲሉም በወቅቱ ገልጸዋል:: በቀይ ባህር ጉዳይ፣ በዓባይ ግድብ ላይ እንዳለው መደራደር እንደሚቻልም አመልክተው፤ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የመሆን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚ ጭምር መሆኑን ተናግረዋል::

ለመሆኑ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት መሆን የምትችለው እንዴት ነው? ለዚህስ ስኬት ከወዲሁ ምን እየተሰራ ነው? ስንል እኛም የዘርፉን ተመራማሪዎች አነጋረናቸዋል:: ካነጋገርናቸው ተመራማሪዎች አንዱ የሆኑት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲቲዩት መሪ ተመራማሪና የመካከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር ጀነራል ዶክተር አማረ ቀናው ናቸው:: ዶክተሩ፣ አንድ ሀገር የባህር በር እንደሚያስፈልገው ይታወቃል ይላሉ:: የባህር በር ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለብሔራዊ ጥቅም እንዲሁም ለደህንነትም ጭምር አስፈላጊ እንደመሆኑ እነዚህን ለማስጠበቅ የሚጠቅም እንደሆነም ያመለክታሉ::

የባህር በር ለማግኘት በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል:: አንደኛው ሙሉ በሙሉ ከባህር ጋር የሚያገናኘው ወደብ በባለቤትነት ወይም የራስ የሆነ መሬት ማግኘት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የባህር በር ተጠቅሞ የአንድን ሀገር ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ናቸው::

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ወደብ የላትም:: እየተገለገለች የምትገኘው የሌሎችን ወደብ ተከራይታ ነው:: በዚህ መልኩ መቀጠል የሚያስከፍለው መስዋዕትነት ብዙ ነው:: ከዚህም የተነሳ አሁን ጉዳዩ ተነስቷል:: ጥያቄው ቀድሞም ቢሆን ተዳፍኖ በእያንዳንዱ ልብ የተቀመጠ ነው ሲሉ ዶክተሩ ይናገራሉ::

እንደ ዶክተር አማረ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት የምትችለው በቀጣናዊ ትብብር ነው:: ለዚህ ደግሞ ኮንፈረንሶችን ማዘጋጀትና በጉዳዮች ላይ መነጋገር መልካም ነው:: በተለይም ተፈጥሯዊ የሆነው ይህን ሀብት



አማረ ቀናው (ዶ/ር)



ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር)

በእኩልነት እንዴት ማስተዳደር እንችላለን? የሚለውን ለማጠናከር ቀጣናዊ ትብብሮችን በአግባቡ ማጠናከር አስፈላጊ ነው::

ከዛ በመነሳት ደግሞ የትብብር ማዕቀፎችን ዲዛይን ማድረግ ያስፈልጋል:: ከዚህ ጎን ለጎን ተጠቃሚነትም መኖር አለበት:: ጉዳዩ ገና ሲነሳ «ውሃችንን ልትወስዱ ነው» ከመባባል ባለፈ የጋራ ተጠቃሚነታችንን ጉዳይ እንዴት አድርገን ነው ማጠናከር ያለብን በሚለው ላይ መወያየት መልካም ነው:: የጋራ ተጠቃሚነት ከሌለ ግጭቶች ይኖራሉ:: ግጭት ደግሞ ከቀጣናው ውጭ ያሉትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነውና ይህንን ጉዳይ ሁሉ ለመቆጣጠር ቀጣናዊ ትብብር ወሳኝ ነው::

ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ቀጣናዊ ትብብር ብዙ ጠንካራ የሚባል አይደለም:: ስለዚህም ማጠናከር ያስፈልጋል:: ከማጠናከር አኳያ ሲታይ ደግሞ ከዚህ በፊት ጠንካራ ሚና ስትጫወት የነበረች ኢትዮጵያ እንደመሆኗ ከዚህ በኋላ ለሚደረገውም ትብብር ተነሳሽነቱን ወስዳ ልትሰራ ያስፈልጋል ሲሉ ዶክተር አማረ አስረድተዋል::

ሌላው ያነጋገርናቸው በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት መሪ ተመራማሪ እና የኢስያ ፓስፊክ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር ጄኔራል ዶክተር ዳርእስከዳር ታዬ ናቸው:: እርሳቸው ኢትዮጵያ እያደገ ከሚሄደው የሕዝብ ቁጥሯና ኢኮኖሚዋ ጋር ተያይዞ የባህር ባር ያስፈልጋታል ይላሉ:: ከፍ ያለ የሕዝብ ቁጥር ያላት ኢትዮጵያ በአንድ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆና መቀጠል እንደማትችልም ይናገራሉ::፣

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ካለፉት 30 ዓመታት ጀምሮ በአንድ ወደብ ላይ ጥገኛ ሆና ዘልቃለች:: ይህ ከነበረው የሕዝብ ቁጥርና የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር ብዙም ተጽዕኖ ሳያመጣ ዛሬ ላይ መድረስ ተችሏል:: አሁን ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ጨምሯል:: ኢኮኖሚዋም በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል ፊተኛውን መስመር ይዟል:: ስለዚህም አሁን ካለከውና በቀጣይ ከሚኖረውም ግዙፍ ኢኮኖሚ አንጻር አንድ ወደብ ብቻ ገቢና ወጪ ዕቃዎችን ሊያስተናግድ አይችልም::

ኢትዮጵያ የባህር በር ያስፈልጋታል ሲባል ብዙዎች ጉዳዩን ከጦርነት ጋር ያያይዙታል የሚሉት ዶክተር ዳርእስከዳር፣ እንደዚያ ማሰቡ አግባብነት የሌለው መሆኑን ያመለክታሉ:: አማራጮቹ በርካታ መሆናቸውን በመጥቀስ ለአብነት ያህል በኪራይ ተጨማሪ ወደቦችን ማግኘት አሊያም ወደብ በጋራ ማልማት ወይም ደግሞ የአካባቢ ልውውጥ በማድረግ እንደሚቻል ያስረዳሉ::

ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ እያከናወነቻቸው ካሉ ልማቶች ውስጥ የተወሰኑትን በመስጠት እና በምትኩ ወደብ በማግኘት ማካካስ ይቻላል ሲሉም ይገልጻል:: እንዲያም ሲባል ከህዳሴ ግድብ ተርባይኖች ውስጥ የተወሰኑትን በመስጠት ወደብ በምትኩ ማግኘት ተጠቃሽ እንደሆነ ይናገራሉ::

ለአብነትም ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባህር በር አላት:: ግን ይህ ሁሉ ኪሎ ሜትር ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም:: ስለዚህም ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች ወደብ ከኢትዮጵያ ጋር ማልማት ትችላለች:: ወይም ደግሞ ለም መሬት ወስዳ በምትኩ ወደብ ልታቀርብልን ትችላለች በሚል በርካታ አማራጮች እንዳሉ ዶክተር ዳርእስከዳር ያመለክታሉ::

ስለወደብ ጉዳይ ሲነሳ እኛም የባህር በር ሊያጋሩን የሚችሉ ሀገራትም የተቸከሉት መሬት በሚለው ላይ ጉዳይ ላይ ነው የሚሉት ዶክተር አማረ በበኩላቸው፤ በዚህ ላይ ብቻ መንጠልጠል ሳይሆን የባህር በር የሚገኝበትን አማራጭ ማስፋት ይቻላል ይላሉ::

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ከብዙ መንገዶች አንዱ በኮሪዶር መጠቀም የሚለውን ማንሳት ይቻላል:: ለኮሪዶር ደግሞ መሬት ለመስጠት ምንም ችግር የለውም:: እሱ ማለት ዓለም አቀፍ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን እንደመዘርጋት ማለት ነው፡። ኮሪዶር የሚሰራባቸው ሀገሮች አሉ:: ለምሳሌ አዛርባጃን የባህር በር የላትም:: ነገር ግን በሌላ ሀገር ላይ ኮሪዶር በመገንባት የባህር በር ተጠቃሚ የሚሆንበትን እድል ፈጥራለች::

ከዚህ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስተሩ እንዳሉት ሌላ ነገር ሰጥቶ መቀበል ይቻላል:: ይህ ግን በተለያዩ ጥናቶች የሚመለስ ነው ብዬ አስባለሁ:: በጣም ብዙ አማራጮች ስላሉ መንገዱ ዝግ አይደለም:: እንዲያው አንዱ ላይ ብቻ ከምናተኩር የተለያየ ዓይነት አማራጭ ቢኖረን እኛንም ሀገራቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው:: በጣም የሚያስገርመው ነገር ሌሎች ሀገራት ወደአካባቢው ሲመጡ መሬቱም ቢሆን ሲሰጣቸው ይታያል። ለምሳሌ አሜሪካ በብዙ ሺ ማይልስ ርቀት መጥታ ጂቡቲ ላይ መሬት አላት:: ጃፓንና ቻይናም እንዲሁ በብዙ ሺ የሚቆጠር ማይልስ አቋርጠው መጥተው ወይ ጂቡቲ ላይ ወይም ደግሞ ኤርትራ ላይ መሬት አላቸው::

ታዲያ የአፍሪካ ሲሆን ልዩነቱ ምንድን ነው? ሲሉ የሚጠይቁት ዶክተር አማረ፣ ቢሆን የተባለው እንኳ በሊዝ፣ በኮሪዶርና መሰል ነገሮች ነው ሲሉ ያስረዳሉ:: ይህን ማድረግ የሚቻለው ግን ቀጣናዊ የሆነ ትብብር ሲኖር ነው:: ለምሳሌ መሬቱ ለኢትዮጵያ በተለያየ መንገድ ቢሰጥ የሚለው ሃሳብ አልተገዛም:: ለአሜሪካኖቹ አሊያም ለሌሎቹ ሀገራት እንደሚሰጠው ሁሉ ለኢትዮጵያ እንስጥ የሚለው ሃሳብ በሌላውም ዘንድ አልተገዛም:: እኛም እስካሁን አልገዛነውም:: ይህ በጥናት መደገፍ አለበት ይላሉ::

ዘይላ ሶማሊያ እንደሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባህር በር ነው የሚሉት ዶክተር ዳርእስከዳር፣ ደግሞ ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም መኖሯን ያስታውሳሉ:: ስለዚህ ለኢትዮጵያ ቅርበት ያለው ዘይላ ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት እንደማትችል ጠቅሰው፤ ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ ሲሉ አስረድተዋል::

እንደ እርሳቸው አባባል፤ በተመሳሳይም ከኤርትራ ጋር በተፈጠረው መልካም የሰላም አጋጣሚ የአሰብን ወደብ በሰላማዊ አማራጭ ለመጠቀም ውይይት ማድረግ ይቻላል:: በምትኩ ደግሞ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የምትፈልጋቸው አቅርቦቶች ይኖራሉ፤ እነሱን በመስጠት አሰብን መጠቀም ይቻላል:: በሌላ በኩል የሶማሌ ላንድ ሌላኛው ተጠቃሽ ሲሆን፣ የበርበራ ወደብን በጋራ ማልማትና መጠቀም የሚቻል ነው::

የኢትዮጵያ ማደግ ለጎረቤት ሀገራት ዕድል ይዞ የሚመጣ እንደሆነ የሚያብራሩት ዶክተር ዳርእስከዳር፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያደገ ሲመጣ ተጨማሪ ወደቦች ያስፈልጓታል:: ጎረቤት ሀገራትም ወደቦችን በማከራየት፣ በጋራ በማልማት ወይም ከኢትዮጵያ በሰጥቶ መቀበል መርህ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በማግኘት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ ብለዋል::

ለምሳሌ ሲዊዘርላንድን ብትመለከት የባህር በር የሌላት ሀገር ነች:: ነገር ግን የአካባቢው ሀገራት በጋራ ተጠቃሚነት የሚያምን ስለሆኑ በገበያ ዋጋ ለስዊዘርላንድ ወደባቸውን በቀላሉ እያከራዩ እየተጠቀሙ ነው:: ለእነሱ የወደብ ጉዳይ ብዙም አወዛጋቢ እንዳልሆነ አስረድተዋል::

ታዲያ ወደ አፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሲመጣ ችግሩ ምንድን ነው የሚሉት ዶክተሩ፣ ከአስተሳሰብ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደሚስተዋሉ ያስረዳሉ:: በቀጣናው ከመተባበርና በጋራ ከመሥራት ይልቅ የመከላከልና ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚደረግ ነገር እንዳለ አመልክተው ይህ ግን ወደ ትብብር ቢቀየር ሁሉንም ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይገልጻሉ:: ከትብብር ይልቅ የመገፋፋት ባህሪን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ያመለክታሉ::

በቀጣናው ያሉ ሀገራት ሁሉ ማደግ ይፈልጋሉ:: ስለዚህም አጓጊ ከሆነው የኢትዮጵያ እድገት ለመሻማት እራሳቸውን ማዘጋጀታቸው አይቀርም:: ስለዚህም አሁን ያለውን በመንግሥታት ደረጃ ያለውን ግንኙነት ተቋማዊ ማድረግ ከተቻለና የበለጠ መተማመን ከተፈጠረ የአሰብን ወደብ በጋራ የምንጠቀምበት ሁኔታ አይኖርም ብዬ አላስብም ይላሉ:: ሁሉም ሊያስተሳስረው እና ትብብር ሊፈጥርበት የሚችለው ነገር እንዳለውም ያስረዳሉ:: ከአካባቢው ሀገራት ጋር መነጋገር እና ፍላጎትን ማጣጣም ከተቻለ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ በርካታ አማራጮችም እንዳሉም ይናገራሉ::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይም፣ ስለቀይ ባህር እና ወደብ ጉዳይ ለፓርላማ አባላት በገለጹበት ወቅት፤ የባሕር በር ጥያቄ ኤርትራ፣ ጂቡቲ እና ሶማሌላንድ አማራጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ዘርዝረዋል:: ኢትዮጵያ ካሏት የወደብ አማራጮች መካከል በተለይም በቀዳሚነት ያስቀመጡት ዘይላን ሲሆን፣ ዘይላ ወደብ በሶማሌ ላንድ ግዛት በምዕራባዊ አውደል ግዛት ውስጥ የሚገኝ እና የኤደን ባሕረ ሰላጤን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ተናግረዋል:: በሁለተኛ አማራጭ ነው ያሉት የጂቡቲ ወደብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራ የሚገኘው የአዱሊስ ወደብንም ጠቅሰዋል::

በርግጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ የምትፈልጋቸውንና የሚያመቻትን የወደብ አማራጮችን ብቻ አልዘረዘሩም:: በምትኩ ደግሞ ኢትዮጵያ ወደብን ለማግኘት በምላሹ ከሕዳሴ ግድብ፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲሁም ከኢትዮ-ቴሌኮም ድርሻ ለመስጠት ፍላጎት እንዳላትም አብራርተዋል::

መሪ ተመራማሪዎቹ በየበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ወደብ ያስፈልጋታል:: ወደብ ለማግኘትም በርካታ አማራጮች አሏት:: በእነዚህ አማራጮች ላይ ግን መነጋገር፣ መወያየትና መግባባት ያስፈልጋል:: መፍትሔው ቀጣናዊ ትብብር ነው:: እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን በእኩልነት እንዴት ማስተዳደር እንችላለን? የሚለውን ለማጠናከር ትብብርን በአግባቡ ማጠናከር አስፈላጊ ነው::

በተለይም ዶክተር አማረ እንደሚሉት፤ የትብብር ማዕቀፎችን ዲዛይን ማድረግ ያስፈልጋል:: ተጠቃሚነትም መኖር አለበት:: ጉዳዩ ገና ሲነሳ «ውሃችንን ልትወስዱ ነው» ከመባባል ባለፈ የጋራ ተጠቃሚነታችንን ጉዳይ እንዴት አድርገን ማጠናከር አለብን በሚለው ላይ መወያየት መልካም ነው::

የጋራ ተጠቃሚነት ከሌለ ግጭቶች ይኖራሉ:: ይህ ደግሞ ከቀጣናው ውጭ ያሉትን አካላት ተጠቃሚ ያደርጋል:: በውክልናም በመግባት መንግሥት እስከመመስረት ያደርሳል። ስለሆነም ይህንን ጉዳይ ሁሉ ለመቆጣጠር ቀጣናዊ ትብብር ወሳኝ ነው:: ከማጠናከር አኳያ ሲታይ ደግሞ ከዚህ በፊት ጠንካራ ሚና ስትጫወት የነበረች ኢትዮጵያ ተነሳሽነቱን ወስዳ ቀጣናዊ ትስስሩ እንዲጎለብት የማድረግ ብቃት ያላት ናት ይላሉ::

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ስለ ታዳጊ ሴቶች ...

**ፍሬሕይወት አወቀ**

‹‹ሴትን ልጅ ማስተማር ህብረተሰቡን ማስተማር ነው›› የሚለው አባባል ሴቶች በማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው:: ሴቶች ጥራት ያለው የትምህርት ዕድል ካገኙና ጤናቸው እንዲሁም ደህንነታቸውና መብታቸው ከተጠበቀ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ይታመናል:: ይሁንና በርካታ ሴቶች በብዙ ዕድል ማጣትና ኋላቀር በሆኑ አስተሳሰቦች ምክንያት አቅማቸውን መጠቀም ሳይችሉ ቀርተዋል:: ከዚህም በላይ ሴቶች በብዙ ችግርና ፈተናዎች ውስጥ ሲያልፉ መመልከት የተለመደ ነው::

ሴቶች ከሚገጥሟቸው በርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች መውጣት እንዲችሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚያደርጉት ጥረት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም:: በተለይም የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግና ሴት ልጆች ከሚገጥሟቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መላቀቅ እንዲችሉ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል:: በመሆኑም ዕድሉን ያገኙና ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላቸው በርካታ ሴቶች እንቅፋቶቻቸውን መሻገር ችለዋል:: ከራሳቸው አልፈውም ለሌሎች መነቃቃትን ፈጥረዋል::

የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግና አቅማቸውን አሟጠው መጠቀም የሚችሉበትን ዕድል ከማመቻቸት አንጻር ከሚሠሩ ሥራዎች መካከል ሴት ልጆችን የተመለከቱ የተለያዩ መድረኮች ይጠቀሳሉ:: ለዚህም ዓለም አቀፍ የሴት ልጆች ክብረ በዓል አንዱ ነው:: እኤአ በየዓመቱ ጥቅምት 11 ቀን በሚከበረው (International day of girls) ዓለም አቀፍ የሴቶች ልጆች ቀን ክብረ በዓል በርካታ ጉዳዮች የሚነሱበትና ሴት ልጆች የሚገጥሟቸውን መሰናክሎች ለመቅረፍ ጥረት የሚደረግበትን መንገድ አንድ ማሳያ ነው:: ይህን ክብረ በዓልም ከሰሞኑ ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ከሴቶችና ማህበራዊ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጋር በመተባበር አክብሯል::

በሴት ልጆች መብት ዙሪያ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ፤ (International day of girls) ዓለም አቀፍ የሴቶች ልጆች ቀን ክብረ በዓል የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ሴት ልጆች፣ የወጣት ተወካዮችና ወጣት አምባሳደሮች እንዲሁም የሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት በጋራ በተከበረበት ወቅት መልዕክት ያስተላለፉት የፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መቅድም ጉልላት ናቸው:: ወይዘሮ መቅድም እንዳሉት ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ በሴት ልጆች ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ተቋም ነው::

በተለይም የተለያዩ ግጭቶችና በአየር ንብረት ለውጥ የመጀመሪያዎቹ ተጎጂ የሚሆኑት ሴቶችና ሕጻናት እንደመሆናቸው ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ችግር የሚገጥማቸውን ሴት ልጆች በመታደግ የገጥማቸውን ችግር በመፍታት ወደ ትምህርት እንዲመለሱና በትምህርታቸው፣ በጤናቸውና በሥነ ልቦና የሚገጥማቸውን ችግር ለማቃለል ከመንግሥትና አጋዥ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሠራል::

በሴቶች መብትና ሴቶችን ማብቃት ላይ ትኩረት በማድረግ ዓላማውን ከሚደግፉ የመንግሥት አካላት ማለትም ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባባር በርካታ ሥራዎችን የሚሠራ ተቋም መሆኑን አስረድተዋል:: ተቋሙ በርካታ ፕሮግራሞችን ቀርጾ የሴቶችን ጉዳይ በአጀንዳነት ይዞ የሚሠራ ስለመሆኑ የጠቀሱት ወይዘሮ መቅድም፤ በተለይም የሴቶች ልጆች መብት የተከበረ እንዲሆንና የሚገጥማቸው ማንኛውም የመብት ጥሰት እንዲወገድላቸው ከማድረግ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ይሠራል:: የተለያዩ ግጭቶች፣ ጦርነቶችና የተፈጥሮ አደጋዎች በሚከሰቱበት ጊዜ ደግሞ ዕለት ዕለት የሚታዩት የሴት ልጆች የመብት ጥሰት የበለጠ የሚጎላ በመሆኑ በዚህ ወቅት ሴት ልጆች ለከፋ አደጋ ይጋለጣሉ ነው ያሉት::

እሳቸው እንደሚሉት ሴቶች በተለይም በግጭትና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የሚደርስባቸው ችግርና

**በተለይም ወላጆችና ትምህርት ቤቶች በልጆች አስተዳደግና በስብዕና ቀረጻ ላይ የሚኖራቸው ሚና ጉልህ መሆኑን አንስተው፤ ዛሬ የታዳጊ ሴቶች ትውልድን ማዕከል የሚያደርጉና ተስፋቸውን የሚያደናቅፉ ማንኛውንም ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲቆሙ ማድረግና ማብቃት የሚጠበቅባቸው እንደሆነ ገልጸዋል**

መከራ ለቁጥር የበዛ መሆኑን ተቋሙ በተግባር ማረጋገጥ ችሏል:: በዚህም የመደፈር፣ ወላጆቻቸውን የማጣትና ሌሎች ችግሮችን መመልከት የቻለው ተቋሙ ሴት ልጆች የሚደርስባቸውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችለውን የተለያዩ ሥራዎች እየሠራ እንደሆነም ተመላክተዋል::

ድርጅቱ ሴት ልጆች መብታቸው ተጠብቆ የመማር፣ ጤናቸውን የመጠበቅና ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸው የተሟሉ እንዲሆኑ በተለይም በትምህርት፣ በውሃ ፕሮጀክቶች፣ በሕጻናት ጥበቃና በሌሎችም ተያያዥ ዘርፎች ይሠራል:: በእነዚህና መሰል ፕሮግራሞቹ ሴት ልጆችን፣ ቤተሰቦቻቸውንና አለፍ ሲልም ማህበረሰቡን የሚያግዝ ሥራ እንደሆነ የጠቀሱት ወይዘሮ መቅድም፤ ከዚህ በተጨማሪም የተሻሉና የሚረዱ ፖሊሲዎች እንዲቀረጹ የሚያመላክቱበት የተለያዩ መንገዶች እንዳሏቸው ተናግረዋል::

በሀገሪቱ በሰሜኑ ክፍል ተከስቶ በነበረው ጦርነት በርካታ ጉዳቶች በሴቶች ላይ ስለመድረሱ አስታውሰው በዚህ ዙሪያ የተለያዩ ድጋፍና እገዛ ማድረጋቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ መቅድም፤ ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ሰብዓዊ ድርጅት እንደመሆኑ ለጉዳዩ እጅግ ቅርብ ሆኖ ሲከታተልና የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱን ገልጸዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በጦርነት ምክንያት የተለያየ ጉዳት ደርሶባቸው በመጠለያ ካምፕ የተጠለሉትን ልጆች በማግኘት የደረሰባቸውን ጉዳት፣ ችግር፣ ህመምና ስቃያቸውን ተመልክተዋል:: ተቋሙ እንደ አንድ ሰብዓዊ ድርጅት ተፈናቃዮች በተጠለሉበት መጠለያ ውስጥ ለሚገኙ ልጆች ከንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ጀምሮ የተለያዩ ርዳታዎችን ሲያደርግ ቆይቷል:: ከትምህርት ጋር ተያይዞም እንዲሁ በርካታ ሥራዎችን የሠራ ሲሆን፤ ተቋሙ በተለይም ትግራይ፣ አማራና አፋር ላይ ባሉት ፕሮጀክቶች ያዘኑና የተከፉ ሕጻናት ወደ ደስታና ሳቃቸው እንዲመለሱ የማድረግ ሥራን አበክሮ ሲሰራ መቆየቱን አመላክተዋል::

በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚደርሱ ችግሮች በዓመት አንድ ቀን በሚከበር ክብረ በዓል ብቻ የሚታይና የሚፈታ አይደለም:: የሚሉት ወይዘሮ መቅድም፤ ነገር ግን ቀኑ ሲከበር ያሉትን ችግሮች ማየትና ወደፊት መሠራት ስለሚገባቸው የቤት ሥራዎች መረዳት ያስችላል:: ከዚህም ባለፈ የቀኑ መከበር መፋጠን ስለሚገባቸው ጉዳዮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ዕድል የሚፈጥር እንደሆነ ነው የጠቀሱት፡፤

የሴት ልጆችን ችግር ለማገዝና ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ በርካታ መሰናክሎች የሚገጥሙ እንደሆነ ያነሱት፤ ወይዘሮ መቅድም፤ ከፋይናንስ አቅም ጀምሮ የሚገጥሙ የተለያዩ ችግሮችን በመቋቋም እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል:: እንደሳቸው ገለጻ፤ በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ፈተናዎችን ከባድ የሚያደርጉ ጦርነቶች፣ ግጭቶችና መፈናቀሎች ባሉበት አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ ሰብዓዊ ርዳታና እገዛ ማድረግ መቻል በራሱ ፈተና ነው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሠራተኞችን ደህንነት ጠብቆ ሥራቸውን መሥራት እንዲችሉ ማድረግና ምቹ ሁኔታዎች በሌሉበት ቦታዎች ላይ ጭምር በመገኘት ችግር የገጠማቸውን ሴት ልጆች ለማገዝና ለመደገፍ የሚደረገው ጥረት ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ስለመሆናቸው ነው ያስረዱት::

የሴት ልጆች በዓልን ማክበር የሴቶችን ኃይል፣ አቅምና መብት እንዲከበር ከማድረግ ባለፈ ሴት ልጆች ድምጻቸው እንዲሰማና በሴት ልጆች ትምህርትና መብት ላይ የሚሰሩ አካላት ጭምር የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የሚያስችል ትልቅ በዓል እንደሆነም የፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መቅድም ተናግረዋል::

በዕለቱ የተገኙት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚንስትር አማካሪ ወይዘሮ ዘቢደር ቦጋለ በበኩላቸው፤ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ የሴት ልጆች ቀን (International day of girls) ማክበሩን ጠቅሰዋል:: የክብረ በዓሉ ዋና ዓላማም የታዳጊ ሴቶችን መብት በማስጠበቅ ያላቸውን ዕምቅ አቅም ለመጠቀም፣ ለማብቃትና የበለጠ ዕድሎችን በመፍጠር በአድሏዊ ልዩነቶች ምክንያት የሚደርስባቸውን የተለያዩ ችግሮች መፍታትና የህበረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እንደሆነ አመላክተዋል::

ከዚህም ባሻገር ዓለም አቀፍ የሴት ልጆች ቀን ክብረ በዓል ታዳጊ ሴት ልጆችን የሚያበረታታና ድምጻቸውን የሚያጎላ ታላቅ ሁነት መሆኑን የጠቀሱት ወይዘሮ ዘቢደር፤ ታዳጊ ሴቶች ጾታን መሠረት ካደረገና የወደፊት ህልማቸውን፣ ተስፋቸውንና ህልውናቸውን ከሚያጨልሙ ጥቃቶችና ጎጂ ተግባራት ከተጠበቁ፣ መብታቸው ከተከበረላቸው ያላቸውን ዕምቅ አቅም አውጥተው መጠቀም እንደሚችሉ ነው የገለጹት:: እሳቸው እንደሚሉት ሴቶች ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው እንዲሁም ጥረታቸውን መደገፍ ከተቻለና ካበረታታናቸው በራስ የመተማማንና ጠንካራ ሥነ ልቦና በማዳበር በግል ሕይወታቸው ስኬታማ መሆን ይችላሉ:: ከዚህም ባለፈ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር ደረጃ የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ::

ይሁንና በሀገሪቱ በተለይም በተዛባ በሥርዓተ ጾታ ግንኙነት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ በዘልማድ በሰፊው እየተተገበሩ ባሉ ጎጂ ድርጊቶች፣ ጥቃቶች፣ እንዲሁም በአስፈጻሚ አካላት መካከል የቅንጅታዊ አሰራር መጓደል፣ የአፈጻጸም አቅም ውስንነት በመኖርና የተጠያቂነት አሰራርም በሚፈለገው ደረጃ ባለመድረሱ የተነሳ  ታዳጊ ሴቶች አሁንም ለተለያዩ የመብት ጥሰቶች ይዳረጋሉ:: ያሉት ወይዘሮ ዘቢደር፤ በዚህ የተነሳም ለአዕምሯዊ፣ ለአካላዊ፣ ለሥነ ልቦናዊና ለሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እየተጋለጡ እንደሆነ አመላክተዋል::

በሌላ በኩል ግጭቶችና ተፈጥሯዊ የሆኑ አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሕጻናትና ታዳጊ ሴቶች ከመኖሪያ ቤታቸው የሚፈናቀሉበት፣ የትምህርት ዕድል፣ የጤና፣ የመሠረተ ልማት መጓደል የሚያጋጥሙ ችግሮች እንደሆኑ ጠቅሰዋል:: ከዚህ ባለፈ ልጃገረዶችና ሴቶች ጾታዊ ጥቃት የሚደርስባቸውና በምላሹም ውስብስብ ለሆኑ የማህበረሰብና የሥነ ልቦናዊ ጉዳት እንዲሁም የጤና ዕክሎች የሚጋለጡበት አጋጣሚ የሰፋ እንደሆነ ያነሱት ወይዘሮ ዘቢደር፤

ይህም የታዳጊ ሴት ልጆችን መብታቸውንና ደህንነታቸውን በማስጠበቅ ሁሉንም ዓይነት አድሏዊና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ጥቃቶችን ለማስወገድ የተዘጋጀው የ10 ዓመት ዕቅድ ከዘላቂ የልማት ግብ ጋራ በማያያዝ ተግባራዊ ለማድረግና ለማሳካት የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ አድርጎታል ነው ያሉት:: ስለሆነም ግጭትና መፈናቀል በታዳጊ ሴቶች ሕይወት ላይ በተለያየ መልኩ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ፈርጀ ብዙ በመሆኑና ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ለኃይል ጥቃቶችና የመብት ጥሰቶች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ሁሉም ሰው ለሴት ልጆች የተለየ ጥበቃና ከለላ በማድረግ ሊታገልላቸው እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል::

በተለይም ወላጆችና ትምህርት ቤቶች በልጆች አስተዳደግና በስብዕና ቀረጻ ላይ የሚኖራቸው ሚና ጉልህ መሆኑን አንስተው፤ ዛሬ የታዳጊ ሴቶች ትውልድን ማዕከል የሚያደርጉና ተስፋቸውን የሚያደናቅፉ ማንኛውንም ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲቆሙ ማድረግና ማብቃት የሚጠበቅባቸው እንደሆነ ገልጸዋል:: በተያያዘም ሌሎች ማህበራዊ ወጎችን ከምቹ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር እንዲሁም ከሕግና ፖሊሲዎች ጋራ የተያያዙ ውጤታማ ስልቶችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ታዳጊ ሴቶች የወደፊት የሥራ ዕድሎቻቸውን በማስፋት፣ ሙሉ ተሳትፎ ኖሯቸው የኢኮኖሚ አቅማቸውም እንዲያድግ ለማድረግ ተገቢውን ክህሎትና ስልጠና የታጠቁ እንዲሆኑ አበክሮ መሥራትን የሚጠይቅ እንደሆነ አብራርተዋል::

ለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከክልል መዋቅሮችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ልዩ ልዩ ሁነቶችን በማዘጋጀት እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት ወይዘሮ ዘቢደር፤  በተለይም በታዳጊ ሴቶች መብት፣ በልጃገረዶች ትምህርት ፋይዳ፣ በሥርዓተ ጾታ እኩልነትና ታዳጊ ሴቶች በሚገጥሟቸው ችግሮችና መፍትሔዎች ዙሪያ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር በተቋማት አካቶ ትግበራ ስኬታማነት በትኩረት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል::

ታዳጊ ሴቶች የተጎናጸፏቸው መብቶች እንዲከበሩ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ፣ አቅማቸው እንዲያዳብርና ከፊታቸው የሚጠብቃቸውን ብሩህ የወደፊት ሁኔታ በውል መረዳት እንዲችሉ መሥራት ተገቢ ነው የሚሉት ወይዘሮ ዘቢደር፤ መብትና ደህንነታቸውን ማስከበር፣ ማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋት ዙሪያ የሚሠራው ሥራ አስቸኳይ ተግባር ብቻ ሳይሆን ለሀገር ዕድገት ብልጽግና ብልህ ምርጫ እንደሆነ አጽንኦት በመስጠት ነው የገለጹት::

ዓለም አቀፍ የሴት ልጆች ቀን (International day of girls) በዓለም ለ11ኛ ጊዜ የተከበረ ሲሆን፤ በኢትዮጵያም ‹‹ታዳጊ ሴቶችን እናብቃ መብትና ደህንንታቸውን እናስጠብቅ›› በሚል ሀገራዊ መሪ ሃሳብ ለ10ኛ ጊዜ በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሯል::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

በሆነ ወቅት የተፈጠረን አንድ ጉዳይ ጥሩም ይሁን መጥፎ ዛሬ ላይ ዳግም ባልጠበቅነው አጋጣሚ ድንገት ስንሰማው ወይም ተጽፎ ስናገኘው ቀልባችንን መግዛቱ አይቀሬ ነው። ጉዳዩና ወይም ሁኔታው ሲፈጠር ከነበርን ደግሞ 'ኸረ እኔም እኮ ነበርኩ...' ስንል በኩራት ማውራታችን አይቀርም። ዛሬ ላይ ከብዙ ዓመታት በፊት የተከወነውንና ያሳለፈውን ጉዳይ ድንገት ከዚሁ ዓምድ ላይ ስናገኘው ምን ይሆን የሚሰማን? በአዲስ ዘመን ድሮ ትናንትናዎቻችንን የሚያገኙ ብዙዎች ናቸው። የዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዘመናትን ወደ ኋላ ተመልሶ ‹በደረሰው የባቡር አደጋ በርካቶች ለሞትና ከባድ አደጋ ተጋልጠዋል፣ ታላቁ ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ዘሪሁን በሞት ተነጠቀ› በማለት ያስታውሰናል። አሁኑ ወቅት በጦርነት እየተናጠች ያለችው ሀገረ እስራኤልን መለስ ብለን ሌላኛውን የጦርነት ታሪኳን የሚያስታውሰንን ዘገባም እናስታውሳለን። ከጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎችም ገልጠን እናስታውሳለን።

### በባቡር አደጋ 9 ሰዎች ሞቱ

ከጅቡቲ ወደ ድሬዳዋ ይጓዝ የነበረ አንድ የሕዝብ ማመላለሻ ባቡር የካቲት 29 ቀን 1979 የሐዲድ መስመር ስቶ በመውጣቱ ዘጠኝ ሰዎች ሲሞቱ 37 ሰዎች ደግሞ ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የጅቡቲ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 2 ቀን 1979ዓ.ም)**

### የጓድ ብርሃኑ ዘሪሁን የቀብር ሥነ ሥርዓት ተፈጸመ

የአንጋፋው ጋዜጠኛና የታዋቂው ደራሲ የጓድ ብርሃኑ ዘሪሁን የቀብር ሥነ ሥርዓት ትናንት ሚያዚያ 17 ቀን 1979ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጸመ። ጓድ ብርሃኑ ዘሪሁን የሞቱት ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ57 ዓመታቸው ነው።

**(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 18 ቀን 1979ዓ.ም)**

### በእሥራኤል ጦር አውሮፕላኖች የቦምብ ድብደባ ስምንት ሰዎች ተገደሉ

የእሥራኤል ጦር አውሮፕላኖች በአንድ ሳምንት ውስጥ በደቡብ ሊባኖስ ውስጥ ከትናንት በስቲያ ባካሄዱት የቦንብ ድብደባ ስምንት ሰዎች ሲገደሉ ሃያ ስምንት ደግሞ መቁሰላቸውን ከሥፍራው የደረሰ ዜና ገለጠ።

የእሥራኤል ጦር አውሮፕላኖች ባለፈው ዓርብ በሚይህ ሜይህ አቅራቢያ በሚገኙ የስደተኞች ሰፈሮች ድብደባ በመፈጸም አሥራ አራት ሰዎች ከተገደሉና ሰላሳ ሰባት ከቆሰሉ ወዲህ ስደተኞች ከአካባቢ እንዲወጡ መደረጉን ዜናው በተጨማሪ ያመለክታል።

በሌላ በኩል የአረብ ሊግ በእሥራኤል የጦር አውሮፕላኖች በደቡባዊ የሊባኖስ ውስጥ የፈጸሙት የቦንብ ድብደባ በሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚካሄድ ሽብር መሆኑን በማስመልከት ድርጊቱን በጥብቅ አወገዙ።

**(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 10 ቀን 1979 ዓ.ም)**

### ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

*በሀገራችን አባባል ማርያም የሳመችው የሚባለው ልክ አፍንጫዬ መሐሉ ላይ አለ። ሰዎች እንደሚሉኝ አንዳንድ ጊዜ ሴቶቹ "ውይ ታድለህ ማርያም አፍንጫህን ስማሃለች" ይሉኛል። እኔ ግን በዚህ አባባል አላምንም። ይህ ነገር በእርግጥ ማርያም የሳመችን ነው?

አ-ለማ

- አይደለም። ከመወለድ የሚመጣ ነው። ይህ ነገርም እስከ እድሜ ልክዎ ድረስ አይለቅም። አንዳንዱ ሊሰፋ ወይም ሊጠብ ይችላል። ሐኪሞች ግን በኦፕሬሽን ያስለቅቁታል። ለምን እንደሚያስለቅቁት ልናገር? በእሱ ብዙ ጥንቆላ ስላለበት ነው። እንደየአቀማመጡ ወይም እንደየቦታው ሁኔታ የሰውን ጠባይ ወይም ዕድል ይነግረናል ስለሚሉ ነው። ለምሳሌ ያህል አፍንጫው ላይ ያለውን እንዲህ ይሉታል። "የተጓዥነት ምልክት ነው። አፍንጫቸው ላይ ጥቁር ነገር ያለባቸው ሰዎች አንድ ቦታ አርፈው ከሚሠሩት ሥራ ይልቅ በመዞር ሲራራ ነጋዴ በመሆን የሚሠሩት ሥራ መልካም ውጤት አለው። በአንድ ቦታ ተቀምጦ የሚሠራ ሥራ አይሳካላቸውም" ይላሉ። የእርስዎ ሥራ ምንድነው?

**(አዲስ ዘመን የካቲት 12 ቀን 1979 ዓ.ም)**

*የካቲት 27 ቀን በወጣው ዓምድህ አንዲት የ15 ዓመት ወጣት ነኝ ያለች "ከንፈሬ ትልቅ በመሆኑ እጬኛ እየተመለሰ ተቸገርኩ። ከንፈሬን ምን ላድርገው ?" ብላ ጠይቃ ነበር። አንተም ሐኪሞችን ጠይቂ ምናልባት ሳይችሉ አይቀሩም ብለሃታል። አሁን የምለው በየሆስፒታሉ ከምትንከራተት ቢጤው ከቢጤው ይስማማል እንደሚባለው ሁሉ እኔም ከንፈሬ ትልቅ ስለሆነ "ለንቦጫም አንተን የምንይዘው ከንፈርህን ለመሸከም ነው?" እያሉኝ እጅግ ተቸግሬ ነበር።አሁን ቢጤዬን በማግኘቴ በደብዳቤ ተገናኝተን እንድንጋባ ታደርግልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። ለእኔ ለመጻፍ ብትፈልግ አሰላ ለአቶ ባዩ በየነ ብለህ ብትልክ ይደርሰኛል። ግን እንድትገልጥላት የምፈልገው ቁመተ ረዥም፣ ቀጭን፣ ጠጉረ ሉጫ መሆኔን አስረዳልኝ። አድራሻዋን እንድትገልጥልኝ አሳስብልኝ። በስልክ ቁጥር 158 ልታገኘኝም ትችላለህ።

ባዩ ዘነበ

አሩሲ አሰላ

-እቱ ትባያለሽና ምን ትያለሽ? ከተጋባችሁ የውል አባት ለመሆን ደስ ይለኛል።

**(አዲስ ዘመን ግንቦት 22 ቀን 1979 ዓ.ም)**

### *ፋንታ በየሱቁ ከጠፋ ቆይቶአል። ለምንድነው?

- እኔ ለምን እንደሆነ አላውቅም። ባለቡና ቤቶች ሁሉ እንደድሮው አልሆን አሉን እያሉ የሚያወሩት አለ። የቢራውስ ሜሎቲ ስለቀረ ምን ለማጣጣት የቢራ እጥረት ሊኖር ይችላል። የዚህ የነፋንታ ደግሞ ምን ሆኖ ነው? አምቦ ውሃውስ ቢሆን፤ውስኪስ በኮካ ሆኖ የለ? ሰው የሚያወራው ስላለ ብሔራዊ ሀብት ሚኒስቴር ለእንዲህ አይነት አጋጣሚ ለምን መግለጫ አይሰጥም?

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 13 ቀን 1979 ዓ.ም)**

*አንዲት ሴት ዕቃ ለመግዛት ከመደብራችን መጥታ ዕቃ ጠየቀች። መልሱ የጅምላ ቤት ነው በማለት ከሥራ ጉአደኞቼ ጋር መልስ ሰጠናት። እናንተ በዝባዦች አሁን መብታችን እኩል ነው በማለት ምኑን ልንገርህ ከሰው ልጅ አንደበት በማይወጣ ስድብ ተሳድባ ሔደች። መብት የተሰጠው ለስድብ ያለመሆኑን እባክህን ንገርልኝ?

እድሪስ አህመድ

-እስዋን የሰው ልጅ ላለማድረግ ነው ከሰው ልጅ አንደበት የማይወጣ ስድብ ተሳደበች የምትለው? አንዳንድ መንደር የሚያስቸግሩ ሴቶች ከውጭም ያው ናቸውና መቻል ነው። ንዴታም ደግሞ አለና ይሄንንም አትርሱ። ቆርቁአዡም ተናዷል፤ተቆርቁአዡም ተናደዋል። ይሄም ደግሞ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ስለሚቀር አሁን ዝም እያሉ ማሳለፍ ነው።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 13 ቀን 1979 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## ተመድ በማሊ የሰላም አስከባሪ ኃይሎች ሕይወት አደጋ ላይ መሆኑን አሳወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በማሊ የሚገኘውን ሰላም አስከባሪ ሠራዊቱን ከታቀደው ጊዜ በፊት ማስወጣቱን አስታውቋል። ተመድ የሰላም አስከባሪዎች ሕይወት አደጋ ላይ በመውደቁ በአፋጣኝ ሰላም አስከባሪዎቹን ከማሊ ማስወጣት አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል።

ድርጅቱ የመጨረሻ ሠራዊቱ በቴሳሊት የሚገኘውን ካምፑን ለቆ ያለፈው ቅዳሜ ዕለት መውጣቱን ነው ይፋ ያደረገው። እ.ኤ.አ. በ2023 ዓመት መጀመሪያ ላይ ሁሉም የተመድ እና የፈረንሳይ ወታደሮች ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ የሰጡት የማሊ ወታደራዊ መሪዎች፤ የቴሳሊት ካምፕ በቁጥጥራቸው ስር እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የተመድ ሰላም አስከባሪ ኃይል ለመውጣት "ውጥረት የነገሰበት እና የተበላሸ የጸጥታ አውድ የሠራዊቱ ሕይወት አደጋ ላይ ጥሏል" ሲል በማሊ የሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ተልዕኮ (ሚኑስማ) በሰጠው መግለጫ ተናግሯል።

በማሊ የሚገኘው ጥቂት ዓለም አቀፍ ወታደሮች ባሉበት ሁኔታ ሀገሪቱ እስላማዊ ታጣቂዎችን ጨምሮ በታጠቁ ቡድኖች የከፋ ጥቃት ሊደርስባት ይችላል ተብሎ ተሰግቷል። ከሶስት ዓመታት በፊት ማሊ ውስጥ በተሽከርካሪ ላይ በተፈጸመ የቦምብ ጥቃት ቢያንስ 15 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) ሰላም አስከባሪዎች መቁሰላቸው የሚታወስ ነው።

ተመድ በወቅቱ እንዳስታወቀው፤ የሽብር ጥቃቱ ኢላማ ያደረገው ጊዜያዊ ማዘዣ ጣቢያን ነው። በማሊ የተመድ ሁለገብ የተቀናጀ የማረጋጋት ተልእኮ በትዊተር ገፁ እንዳሰፈረው 15 የሰላም አስከባሪ ሃይሎች ቆስለው ወደ ጤና ተቋም ተወስደዋል።

ተመድ የደረሰውን ጥቃት በፅኑ ማውገዙንና በጥቃቱ ቢያንስ አምስት ሰላማዊ ሰዎች መቁሰላቸውን አናዶኑ በወቅቱ ዘግቧል።



## አሜሪካ ጥያቄ በማቅረቧ እስራኤል የወታደራዊ ዘመቻ እቅዷን አራዘመች

በጋዜጣው ሪፖርተር

እስራኤል በጋዛ ለማድረግ ያቀደችውን የእግረኛ ጦር ዘመቻ በአሜሪካ ጥያቄ መሠረት ማራዘሟን የእስራኤል ጦር አስታውቋል። አሜሪካ፣ እስራኤል በጋዛ ላይ በእግረኛ ጦር ጥቃት ለመክፈት የያዘችው እቅድ እንዲራዘም የፈለገችው፣ ተጨማሪ ኃይሏ መካከለኛው ምስራቅ እስከሚደርስ መሆኑን ገልጻለች።

ነገር ግን አሜሪካ ሌላም ምክንያት እንዳላት የሚጠቁም ዘገባም ወጥቷል። የፕሬዚደንት ባይደን አስተዳደር እስራኤል ጋዛን በእግረኛ ጦር የማጥቃት እቅድ እንድታራዝም የፈለገው ተጨማሪ በሀማስ የታገቱ እንዲለቀቁ እና የሰብዓዊ ርዳታ ጋዛ እንዲደርስ በመፈለግ መሆኑን ሲኤንኤን ዘግቧል።

በሀማስ ተይዘው የነበሩ ሁለት አሜሪካውያን ሰዎች መለቀቅ ከተሰማ በኋላ በሃማስ ተይዘው ያሉት 200 ገደማ ሰዎች ይለቀቃሉ የሚል ተስፋ ሰጥቷል። በጦርነቱ ከእስራኤል ጎን የሆነችው አሜሪካ፣ በመካከለኛው ምስራቅ አቅሟን ለማሳየት እና እስራኤልን ለመደገፍ ሁለት ግዙፍ የጦር መርከቦቿን ወደ ሜድትራኒያን ባህር ማስጠጋቷ ይታወሳል።

ፔንታጎን ከእስራኤል የገዛቸውን ሁለት "አይረን ዶም" የሚሳይል መከላከያ ሥርዓቶችን መልሶ ለመላክ ማቀዱን የመንግሥት ምንጮች መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል። የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ለኮንግረስ አባላት በሰጠው ማብራሪያ የመከላከያ ሥርዓቶችን ለእስራኤል መልሶ ለማከራየት ማቀዱን ተናግሯል።

ፔንታጎን "አይረን ዶም"ን የጉዋምን ግዛት ከቻይና ሚሳይሎች ለመከላከል ሲያጤነው እና ሲሞክረው ቆይቷል። ዋይት ሀውስ ከእስራኤል የሚቀርቡለትን ተጨማሪ የደህንነት ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት እንደሚያሟላ ጠቁሟል።

ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በቀጣናው የአሜሪካን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ከማሳደግ በተጨማሪ ለእስራኤል ጥይቶችን ለመላክ ቃል ገብተዋል። "አይረን ዶም" ከሂዝቦላ ሮኬቶችና ከሀማስ ጥቃት ለመከላከል በአሜሪካ ድጋፍ በጎርጎሮሳዊያኑ 2011 ሥራ ላይ ውሏል።

የእስራኤልና የሃማስን ግጭት ተከትሎ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለጋዛ ስደተኞች የነፍስ አድን ሰብዓዊ ርዳታ ሲያቀርብ መቆየቱ የሚታወስ ነው።

# ስፖርት

## የአዲስ አበባን የማዘውተርያ ስፍራዎች ችግር በጥናት ለመፍታት እየተሠራ ነው

ዓስማየሁ ግዛው

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ምዕራፍ ያከናወናቸውን ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ገምግሟል። ቢሮው የወጣቶች ስዕብና መገንቢያና የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች ላይ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ጥናት አድርጎ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እያደረገ መሆኑንም ገልጿል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በርካታ የስዕብና መገንቢያ ማዕከላት የሚገኙ ሲሆን የተወሰኑት የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችን ያካተቱ ናቸው። ማዕከላቱ በሚፈለገው መጠንና ጥራት ካለመሠራታቸውም በላይ ለታለመላቸው ዓላማ ከመዋል አኳያም ጥያቄዎች ይነሳሉ። የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችም ጥያቄ ከሚነሳባቸው ጉዳዮች ዋንኛው ሲሆን የመጠናቸው ማነስ ብቻ ሳይሆን ከአገልግሎትና ጥራት አንጻር የሚፈለገውን ያህል አይደሉም። የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራ የከተማው ቁልፍ ሥራ መሆኑን ለዚህም ቢሮው ጥናት በማድረግ መታረምና መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች እያስተካከለ መሆኑን አስታውቋል። በዚህ ዓመትም እንደ ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራ ችግሮችን ለመፍታት በትኩረት ይሠራል። የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ቢኖሩም ከአጠቃቀም ጋር ጉድለቶች እንዳሉ በመድረኩ ተነስቷል። ለዚህም የመፍትሄ ጥናት አድርጎ ችግሮችን ለመፍታት እየሠራ ነው። በአሁኑ ወቅት በጥናት የተረጋገጡ 1 ሺ 169 የሚጠጉ ነባርና አዳዲስ የማዘውተርያ ስፍራዎች አሉ። እነዚህ ስፍራዎች በተለምዶ አገልግሎት ቢሰጡም ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ግን የላቸውም።

ቢሮው ከመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሽያጭ በተገኘው ገቢ 12 የህጻናት መጫወቻና የወጣቶች ስፖርት መዘውተርያ ስፍራ እንዲገነባ በማድረግ ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን ጠቁሟል። ቢሮው ባለፈው ዓመት 27 የማዘውተርያ ስፍራዎችን ገንብቶ ማስተላለፍም ችሏል። በዘንድሮ ዓመትም አዳዲስ የማዘውተርያ ስፍራዎችን መገንባት፣ ነባሮችንም በማደስና በመጠገን ወደ ሥራ ማስገባትና ያሉባቸውን ችግሮች መፍታትም ቁልፉ ሥራ ይሆናል። በዝግጅት ምዕራፍ ወቅት ቢሮው 7 አዳዲስ የማዘውተርያ ስፍራዎችን መገንባቱንና አምስቱን ማደሱን በቀረበው ሪፖርት ተመላክቷል።

የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን፤ ስፖርቱ ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችን በመደበኛነት ማስፋፋት ማልማትና አዳዲስ መገንባትና ነባሮችን ማደስ ቢሮው እንደ ቁልፍ እቅድ መያዙን ያብራራሉ። ባለፉት አራት ዓመታት 510 የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችን በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግም ተሞክሯል። ትልልቅ ስታዲየሞችን ኢንተርናሽናል ደረጃ እንዲይዙ ለማድረግ እየተሠራም ነው። ከመንግሥት በጀት በተጨማሪም



የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን፤

ባለሀብቱን በማስተባበር የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችን በማልማትና በመገንባት ወጣቱ አላስፈላጊ ስፍራ እንዳይገኝና ተተኪ ስፖርተኞች እንዲፈጠሩ ለማድረግም እቅድ ተይዟል። የሁሉም ስፖርቶች ማጠንጠኛ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ነው ምክንያቱም ታዳጊዎች፣ ወጣቶችና ክለቦች ልምምድ የሚሰሩበት ውድድር የሚያደርጉበት የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራ አስፈላጊ ይሆናል። እነዚህም የሁለት በአንድ፣ የሶስት በአንድ እና የጥርጊያ ሜዳዎች በየአካባቢው እንዲለሙ በፍጥነት በመገንባት ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ በስፋት መሠራታቸውንም ጠቅሰዋል።

ከስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች ጋር ተያይዞ የተከናወኑ ስራዎች የመኖራቸውን ያህል ጉደለቶችም እንዳሉ ያነሱት አቶ በላይ፤ ለምተው ለአገልግሎት የሚተላለፉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ከአጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለታለመላቸው ዓላማ ከማዋልና ለአገልግሎት ክፍት ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች መኖራቸውን ይገልጻሉ። እነዚህን ክፍተቶች ለመመለስ ጥናቶች እንደተጠናቀቁና በየደረጃው ባለው ተቋም አሠራርና ሕግ ከጸደቁ በኋላ ወጥነት ባለው መንገድ ወደ ሥራ እንደሚገባም ተመላክቷል።

ቦታዎቹ እንዴት ይተዳደሩና በማን መተዳደር እንደለባቸው በጥናት ከተለየ በኋላ ሥራቸውን በአግባቡ መሥራትና ለታለመላቸው ዓለማ እንዲውሉ ይደረጋልም ብለዋል። የሀገርን ባንዲራ በዓለም አደባባይ ለማውለብለብ የተተኪ ስፖርተኞች ሚና ወሳኝ በመሆኑ ይህ በሁሉም የከተማው ፌዴሬሽኖችና አሶሴሽኖች የታዳጊ ፕሮጀክቶችና ወጣቶች ውድድር ደረጃና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚሆኑት ወጣቶችን ሲያሳትፉ በመሆኑ ከአገልግልግሎት አሰጣጥ ጋር መታረምና መስተካከል ያለባቸውን ጉዳዮች በዓመቱ በትኩረት ይሠራሉ።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር 001/2016

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የየካቲት 23 አጠቃላይ 2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1 የደንብ ልብስ ፣ የስፖርት ትጥቆች — የጨረታ ማስከበሪያ ብር 7500.00
ሎት 2 አላቂ የቢሮ እቃዎች፣ — የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000.00
ሎት 3 የስፌት የእጅ ዋጋ፣ — የጨረታ ማስከበሪያ ብር 2500.00
ሎት 4 አላቂ የፅዳት እቃዎች፣ — የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5500.00
ሎት 5 ቋሚ የቢሮ እቃዎች፣ — የጨረታ ማስከበሪያ ብር 750.00

በዚሁ መሰረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የምታሟሉ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በጨረታው እንድትሳተፉ ይጋብዛል፡፡

- በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉ -ናሙና /ሳምፕል/ ለሚፈለግባቸው እቃዎች ማቅረብ የሚችሉ
- የተጨማሪ እሴታ ታክስ /ቫት/ ተመዝጋቢ የሆነ ማስረጃ የሚያቀርብ -የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /ቲን ነምበር/ ያላቸው
- በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከዋጋ ማቅረቢያ ጋር በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ቢሮ ቁጥር 2 ለዚህ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
- የጨረታው አሸናፊዎች ማሸነፋቸውን ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ 7 /ሰባት/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የውል ማስከበሪያ ባሸነፉባቸው እቃዎች ላይ 10 ፐርሰንት በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝና ተዋውለው እቃዎቹን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች የሚያቀርቡትን ናሙናዎች ጨረታ ከመከፈቱ ከ 2 ቀን በፊት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በገዙት ሰነድ ላይ ባለው ዋጋ ማቅረቢያ ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ጨምሮ በመግለፅ ዋናውን እና ኮፒውን በመሙላት በታሸገ ኤንቨሎፕ ላይ በተጠቀሰው የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት ቢሮ ቁጥር 2 ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
- በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ አካላት ሲሆን ሰነድ ለመውሰድ በሚመጡበት ጊዜ ከሚመለከተው አካል ወቅቱን የጠበቀ በፅህፈት ቤቱ ስም የተፃፈ የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪ መወዳደር የሚችሉት በራሳቸው በተመረተ ምርት ብቻ ይሆናል፡፡
- ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት ከ 2፡30 – 10፡00 ሰዓት ድረስ የካቲት 23 አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቢሮ ቁጥር 3 በመገኘት የማይመለስ 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
- ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም
- ትምህርት ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ለ10 ተከታታይ የስራ ቀን ቆይቶ በ10ኛው ቀን 11፡00 ሰዓት ላይ የሚታሸግ ይሆናል፡፡
- ጨረታው በጋዜጣው በወጣበት 11 ቀን የስራ ቀን ሆኖ ከዋለ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ላይ የሚከፈት ይሆናል፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር**:- 0112303054/0112768120 መጠየቅ ይቻላል፡፡

**አድራሻ** ፡- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ከአውቶቡስ ተራ ወደ መሳለሚያ በሚወስደው መንገድ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኮልፌ ቅርንጫፍ አጠገብ የካቲት 23 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**
**የየካቲት 23 አጠቃላይ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት**